# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 153 የካቲት 3 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





ፎቶ:ሃይሽ አበርሃ

# የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል

## በአዲስ አደረጃጀት ሊቋቋም ነው

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል በአዲስ አደረጃጀት ሊያቋቁም መሆኑ ተገለጸ። የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል የፖሊሲ አውጪ ባለሙያዎች ጉባዔ እየተካሄደ ነው።

የመከላከያ ውጭ ጉዳይ ግንኙነት እና ወታደራዊ ትብብር ዳይሬክቶሬት ዋና ዳይሬክተር ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ገመቹ በውይይቱ እንዳብራሩት፤ የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል በአዲስ አደረጃጀት ሊያቋቁም ነው። በታሰበው መልኩ የሚቀርቡ ጉዳዮች ውሳኔ ካገኙ የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል ለሚቀጥሉት አሥር ዓመታት በአፍሪካ ቀንድ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በሚገባ እንዲወጣ የሚያስችለው ይሆናል።


የምሥራቅ አፍሪካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# «የዓባይ ግድብ ቱር»

## የጉዞ መርሐ-ግብር በ36 ከተሞችና በ200 ወረዳዎች ይካሄዳል

- የግድቡን ቀሪ ስራ ለማጠናቀቅ 60 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- ለታላቁ ዓባይ ግድብ የገቢ ማሰባሰብ የሚውል "የዓባይ ግድብ ቱር" የተሰኘ የጉዞ መርሐ ግብር በ36 ከተሞችና 200 ወረዳዎች እንደሚካሄድ የታላቁ የኢትዮጵያ ዓባይ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

ቀሪውን የግድቡን ስራ ለማጠናቀቅ 60 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ተገልጿል። የግድቡ ግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አረጋዊ በርሄ በጉዞው ማስጀመሪያ መርሐ-ግብር ላይ እንደገለጹት፤ የሕዝብ ንቅናቄን ለመፍጠርና የተጠናከረ ገቢን ለማሰባሰብ ያለመው የጉዞ መርሐ-ግብር ለሁለተኛ ጊዜ ይካሄዳል።

መርሃ ግብሩ በአዲስ አበባ የተጀመረ ሲሆን፤ በቀጣይም በተለያዩ ከተሞችና ወረዳዎች ይካሄዳል። ግድቡ ብዙ ጫናና ጠላቶች ቢኖሩበትም ችግሮቹን ተቋቁመን በራሳችን ገንዘብ፣ ጉልበት እና ጥረት


«የዓባይ ግድብ ቱር» ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል




ፎቶ: ኢዮብ ተፈሪ


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር




በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም

- 0111 26 26 27
- 0111 26 26 28
- 0111 26 26 29
- 0111 26 26 30
- 0922 11 53 24/26
- 0922 72 74 48/49
- 0922 72 38 70
- 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ








ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል::

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




አቶ ደበበ ዘውዴ

## በሁለተኛው ዙር 107 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ የሰብዓዊ ድጋፍ ቀርቧል

- ከስምንት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ድጋፍ ይፈልጋሉ


ገጽ 4









## ዩኒቨርሲቲው አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየሰራ ነው


ገጽ 11







# ክልሉ ከ9 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥና የውጪ ጎብኚዎችን አስተናግዷል

## - ከቱሪዝም ዘርፉ 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገቢ ተገኝቷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት 9 ሚሊየን 296 ሺህ በላይ የውጭና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን ማስተናገዱን የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።ክልሉ ከቱሪዝም ዘርፉ 2 ቢሊዮን 494 ቢሊዮን ብር ገቢ ማግኘቱ ተገልጿል።

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አባይነህ መንግስቴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ባለፉት ስድስት ወራት ዘጠኝ ሚሊዮን 284 ሺህ 909 የሀገር ውስጥ እና 11 ሺህ 364 የውጭ ሀገር ጎብኚዎች የክልሉን የቱሪዝም መስህቦች ጎብኝተዋል።

አቶ አባይነህ እንዳስታወቁት፤ አጠቃላይ የጎብኚዎች ቁጥር ከታቀደው አኳያ በቂ ባይሆንም በክልሉ አንጻራዊ ሰላም መገኘቱ ቱሪዝም እንዲነቃቃ አድርጓል።

እንደ ሀገር ባለፉት ጊዜያት በነበረው አለመረጋጋት የቱሪዝም ዘርፉ እንደሌሎች ዘርፎች ሁሉ ተዳክሞ እንደነበር የጠቆሙት የቢሮው ምክትል ኃላፊ፤ በተገኘው ሰላም ባለፉት ጊዜያት በክልሉ የሚገኙ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ የቱሪዝም ሀብቶች ለጎብኚዎች ምቹ እንዲሆኑ በተሰራው መጠነ ሰፊ ሥራ ጥሩ ውጤት ተገኝቷል ሲሉ ገልጸዋል።

ክልሉ በርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ እንዲሁም የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ የቱሪዝም መስህቦች ባለቤት ነው ያሉት አቶ አባይነህ፤ ከሐምሌ ወር ጀምሮ የሻደይና አሸንድዬ ሶለን በዓላት፣ የዘመን መለወጫና የመስቀል በዓል፣ የላሊበላ ገና እና በጎንደር ከተማ የጥምቀት በዓላት፣ የአገውና የደብረታቦር የፈረስ ጉግስ በዓላት በርካታ ጉብኚዎችን መሳብ የቻሉ መዳረሻዎች መሆናቸውን አስረድተዋል።

የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ በባህርዳር ዙሪያ የጣና ሀይቅ ገዳማት፣ የጭስ አባይ ፏፏቴ እንዲሁም በቅርቡ የተከበሩ በዓላት እንዲሁም ሌሎች መስህቦችን ከጎበኙ ሰዎች በስድስት ወራት ውስጥ ከ2 ቢሊየን 494 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

አቶ አባይነህ እንዳስታወቁት፤ በክልሉ የጎብኚዎችን ቆይታ ለማራዘም በተቀናጀ መንገድ የመዳረሻ ቦታዎችን ለጎብኚዎች ምቹ የማድረግ ማሻሻያ ዕቅድ ተዘጋጅቷል።

መዳረሻዎችን ለጎብኚዎች ምቹ የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።በዚህም ለቱሪዝም ዘርፉ ማደግ የሚረዱ ስራዎችን በፋይናንስ አቅርቦት፣ በትራንስፖርትና የመንገድ አማራጭ የማስፋት እንዲሁም የሆቴል አገልግሎቶች ዘርፍ ማሳደግ የሚረዱ ጥረቶች እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

በሌላ በኩል የሀገር ውስጥ ቱሪዝሙን ለማሳደግ የሚረዳ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን እና ወንድማማችነት ለማሳደግ ትኩረት ተደርጓል። ቱሪዝሙ ለሰላም ግንባታ አይነተኛ ሚናውን እንዲወጣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመስራት መታቀዱን ምክትል ቢሮ ኃላፊው አስረድተዋል።

በቀጣይ ወደ ክልሉ ለሚመጡ ጎብኚዎች ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ለአድዋ ድል በዓልና ለተለያዩ ክንውኖች የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል ከወዲሁ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል ሲሉም አስታውቀዋል።





ፎቶ - በሳሙኤል ተሰፋዬ

# ሁለተኛው ዙር የኢፕድ የአርታኢያን መድረክ ተካሄደ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአርታኢያን መድረክ የተነሱት ሃሳቦች ከድርጅቱ አልፎ ለሌሎች የሚዲያ ተቋማት ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው ሲሉ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ ገለጹ። ሁለተኛው ዙር የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአርታኢያን መድረክ ትንናት በድርጅቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በውይይት መድረኩ እንደተናገሩት፤ በርዕስ አጻጻፍ፣ አጀንዳ ቀረፃ እና በጋዜጣ ዲዛይን ዙሪያ የተነሱት ሃሳቦችና ጽሁፎች ተቋሙ እያደረገ ላለው ሪፎርም ግብዓት የሚሆኑ በመሆናቸው መድረኩ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በውይይቱ የተነሱት ሃሳቦች ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አልፎ ለሌሎች የሚዲያ ተቋማት ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ የተነሱት ሃሳቦች በፍጥነት ወደ ተግባር እንዲቀየሩ ሁሉም አርታኢያን የበኩላቸውን እንዲወጡ እና በመድረኩ የተነሱት ሃሳቦች ሰፊ ጥናት ተደርጎባቸው ወደ ተግባር እንዲለወጡ አቅጣጫ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የይዘት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ በበኩላቸው፣ በአርታኢያን መድረኩ የተነሱት ሃሳቦችና ጽሁፎች የድርጅቱ ትምህርታዊና ፋይዳቸው የላቀ በመሆኑ ውይይቱ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በተቋሙ ይዘቶች ላይ የተጠቀሱት ድክመቶች በቀጣይ ተሻሽለው እንደሚቀርቡና የታዩት ጥንካሬዎች ደግሞ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

በመድረኩ አጀንዳ ቀረፃን የርዕስ አጻጻፍ እንዲሁም ዲዛይንና ሌይአውትን የተመለከቱ የጥናት ጽሑፎች በድርጅቱ አርታዕያን ቀርበው ሰፊ ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን፤ ጠንካራ ጎኖችን አጎልብቶ ለማስቀጠልና ድክመቶችን ለማሻሻል በግብዓትነት ጥቅም ላይ እንደሚውሉም በማጠቃለያው ተገልጿል።

# 6 ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የንፁህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት ለ6 ሚሊዮን ዜጎች የንፁህ መጠጥ ውሃ ለማዳረስ የሚረዱ ፕሮጀክቶች ግንባታ ላይ መሆናቸውን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ታምሩ ገደፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በ2015 ዓ.ም እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ ድረስ 18ሺህ የውሃ ተቋማትን በመገንባት ለ6 ሚሊዮን ዜጎች ንፁህ ውሃ ለማቅረብ እየተሰራ ይገኛል።

እንደ ሀገር ያለውን የ62 ነጥብ 47 በመቶ የንፁህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነት በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 69 በመቶ ከፍ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን አቶ ታምሩ አስታውቀዋል። በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተያዘውን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ፕሮጀክቶች በተለያዩ ከተሞች እየተገነቡ ይገኛል።

በአንድ ቋት የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን (one wash) ፕሮግራም በ307 ወረዳዎችና በ64 ከተሞች ላይ፤ እንዲሁም በድርቅ በተጎዱ አካባቢዎችም ላይ ባተኮረ ፕሮግራም የንፁህ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ 35 የውሃ ተቋማት ግንባታ ላይ ናቸው ብለዋል።

በእስካሁኑ ግንባታ የተጠናቀቁና በሂደት ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች አሉ። በድምሩ 84 የውሃ ፕሮጀክቶች የየራሳቸው በጀት ተመድቦላቸው ካለፉት 2 ዓመታት ጀምሮ ስራቸው እየተከናወነ እንደሆነ ሥራ አስፈፃሚው አብራርተዋል።

በኢትዮጵያ የሚስተዋለውን ፈጣን የከተሞች መስፋፋት ተከትሎ ንፁህ የመጠጥ ውሃን ተደራሽ ለማድረግ በከተሞች ላይ ብቻ በሚሰራበት "ባስኬት ፈንድ" (Basket Fund) ፕሮጀክት 38 የውሃ ተቋማት ግንባታ ላይ ሲሆኑ፣ 8ቱ ቀደም ስል ተጠናቀው አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

በተጨማሪ በአፍሪካ ልማት ባንክ የሚደገፉ አራት ፕሮጀክቶች በጎዴ፣ ቢቾና፣ አዳማ፣ መቀሌ ላይ መኖራቸውን ጠቁመዋል። ከእነዚህም የአዳማና ቢቾና ውሃ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፤ የጎዴው ፕሮጀክት ደግሞ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል ብለዋል።

አሶሳ፣ ጎንደር፣ ኮምቦልቻ፣ ሚዛን አማን፣ ድሬዳዋና ደብረ ማርቆስ በዋናነት በተዘዋዋሪ ፈንድ የሚገነቡ የውሃ ፕሮጀክቶች አላቸው ያሉት አቶ ታምሩ፤ በየከተሞቹ የሚገኙ የውሃ ፕሮጀክቶች በግንባታና የማስፋፋት ስራ ላይ እንደሚገኙ አስረድተዋል።

አዲስ አበባን ጨምሮ በ23 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት እየተተገበረ ሲሆን፤ በዋነኛነት ስራው የውሃ ብክነትን በመቀነስ ለኅብረተሰቡ ንፁህ ውሃን ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዝ ስራ መሆኑን ጠቁመዋል።

መቀሌን ጨምሮ በግጭት ምክንያት የተጎዱ አካባቢዎችን በመለየት የተቋረጠውን የንፁህ አገልግሎት ለማስቀጠል ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ለመግባት እንቅስቃሴዎች እየተደረገ ነው ብለዋል።

አቶ ታምሩ እንዳስታወቁት፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በግጭት በተጎዱ የትግራይ፣ አፋርና አማራና አካባቢዎች እንዲሁም በተለያዩ መለስተኛ ከተሞች ላይ ሰፊ ስራ ለማከናወን ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እየሰራ ይገኛል።

በተጨማሪም በድንበር አካባቢ በሚገኙ ወረዳዎች ላይ ትኩረቱን ያደረገው የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ የጥልቅ ውሃ ፕሮጀክት በ2015 በጀት ዓመት በ55 ወረዳዎች ተግባራዊ ለማድረግ ስራዎች ተጀምረዋል። ፕሮጀክቱ ለሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት እየተጠናከረ ይቀጥላል ብለዋል።

በኅብረተሰቡ መሪነት በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰሩ ስራዎችን ለመደገፍ ከፊንላንድ መንግስት በተገኘ ድጋፍ በ104 ወረዳዎች ላይ የምንጭ ማጎልበትና መለስተኛ የውሃ ተቋማት ግንባታ እየተከናወነ መሆኑን አቶ ታምሩ ገልጸዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የንፁህ ውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል የሚረዱ ከ207 ሺህ በላይ ከአነስተኛ እስከ ትላልቅ የውሃ መሰረተ ልማቶች እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

# ዩኒቨርሲቲው የፈጠራ አቅሙን አሟጦ እንዲጠቀም ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

በሪሁ አረጋ




አዲስ አበባ፡- አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የፈጠራ አቅሙን አሟጦ እንዲጠቀም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በትናንትናው ዕለት የስድስት ወር የሥራ አፈጻጸሙን ለሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው ባቀረበበት ወቅት፣ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶክተር ነገሪ ሌንጮ እንደተናገሩት፤ ዩኒቨርሲቲው የፈጠራ ሥራዎችን በማሳደግ ረገድ ጉልህ ሚና ቢኖረውም ያለውን እምቅ አቅም በሙሉ አሟጦ እየተጠቀመ አይደለም ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው በቴክኖሎጂ ፈጠራ ሥራዎች አቅም ያላቸው መምህራንና ተማሪዎች አሉት ያሉት የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው፤ ይህንን አቅም እንደምቹ ሁኔታ በመጠቀም የፈጠራ አቅሙን የበለጠ በማሳደግና በአግባቡ በመጠቀም ማሕበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ እንዳለበትም አስታውቀዋል።

ቋሚ ኮሚቴው፤ ዩኒቨርሲቲው ከአዳማ በተጨማሪ ወደ ሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ያሉ ማሕበረሰቦችን ማገልገል የሚያስችል አቅም እንዳለው ከቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቶቹ መረዳት የሚቻል ቢሆንም በዚያው ልክ ግን በሙሉ አቅሙ እየተንቀሳቀሰ አይደለም ተብሏል።

ዩኒቨርሲቲው የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ከመስራት አኳያ የግንባታና የጥገና ሥራዎች ላይ ባቀረበው ሪፖርት በጥቅሉ ሲታይ የተሻለ አፈጻጸም ማስመዝገቡን የተናገሩት የተከበሩ ዶክተር ነገሪ፤ ነገር ግን መስተካከል ያለባቸው እጥረቶች እንዳሉትም አስረድተዋል።

በልማት ፕሮጀክቶች ግንባታና ጥገና ላይ እንደ ክፍተት የተለዩ ጉዳዮች በሚቀጥሉት ስድስት ወራት እቅድ ውስጥ ተካትተው ለማረም በትኩረት እንዲሰራም የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አሳስበዋል።

እንደ ዶክተር ነገሪ ማብራሪያ፣ ዩኒቨርሲቲው በምርምር፣ በፈጠራና በቴክኖሎጂ ሽግግር ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ለማበርከት ከተጣለበት ኃላፊነት አኳያ በኢትዮጵያ የታዳሽ ኃይል አቅም በጥናት የመለየት ሥራ ላይ ብዙም አልገፋበትም። በፈጠራ ዘርፉም በሀገር አቀፍ የሥራ ፈጠራ ውድድር ላይ ተማሪዎችን ለማሳተፍ የያዘውን እቅድም በአግባቡ አላከናወነም። በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶች በቀጣይ ጊዜያት በትኩረት እንዲሰራ ማሳሰቢያ ተሰጥቶታል።

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ለሚ ጉታ የስድስት ወር እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት እንደገለፁት፤ ዩኒቨርሲቲው ከቋሚ ኮሚቴው የተሰጠውን ማሳሰቢያ በቀጣይ ለማረም እንደሚሰራ ተናግረዋል።



# «የጋራ መኖሪያ ቤት የውል ሂደት ለእንግልት ዳርጎናል»

- የጋራ መኖሪያ ቤት ዕድለኞች

# «መጨናነቁ የተፈጠረው በተቀመጠላቸው ጊዜ ባለመገኘታቸው ነው»

- የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ14ኛ ዙር የ20/80 እና ሦስተኛ ዙር 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤት ዕድለኞች የውል ሂደቱ ላይ ያለው መጨናነቅ ለእንግልት እንደዳረጋቸው ተናገሩ።

አገልግሎቱን በመጠቀም ሂደት ላይ ያገኘናቸው አቶ ዮሐንስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአገልግሎት ማዕከሉ ሁሉም ነገር ለእይታ በሚመች መልኩ በግልጽ መለጠፉ መደናገርን የሚቀርፍ ቢሆንም አገልግሎቱን ለማግኘት ረጅም ወረፋ ለመጠበቅ ተገደዋል።

የውል ሂደቱ ግልጽ ቢሆንም የተገልጋዮች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ አገልግሎቱን ለማግኘት ለረጅም ሰዓት ወረፋን ለመጠበቅ ተገድደዋል። በተጨማሪም የፋይል አከፋፈትና አያያዝ ችግር፣ የሀገር ውስጥ ውክልና አለመስተናገድ እና የተቀመጠው የጊዜ ገድብ አጭር መሆን ለወከባና ለእንግልት ዳርጓቸዋል።

አቶ ሳሙኤል ተክለአብ የተባሉት ተዋዋይ በበኩላቸው፤ ተገልጋዮች በወረፋ መጨናነቅ እየተንገላቱ መሆኑን ጠቁመው፤ ኮርፖሬሽኑ የተገልጋዮችን እንግልት ለማስቀረት በትኩረት እንዲሰራ ጠይቀዋል። ያለው ውክቢያና ትርምስ ተገቢ የሆነ መፍትሄ ይሻልም ብለዋል።

ሌላኛዋ የቤት እድለኛ ወይዘሮ መቅደስ ጌታቸው እንደተናገሩት፣ በተያዘላቸው የቀነ ገደብ ቢገኙም በተስተናጋጁ ቁጥር መብዛትና የአሰራር ሂደቱ ቀልጣፋ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ አገልግሎቱን ማግኘት አልቻሉም። ኮርፖሬሽኑ ባወጣው ፕሮግራም መሰረት ደንበኛውን ማገልገል እንደማይቻልም ለመታዘብ ችለዋል። አሁን ባለው ሁኔታ የተቀመጠው የርክክቡ ሂደት ቀነ ገደብ ሳያንስ እንደማይቀርም ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የጋራ መኖሪያ ቤት ማስተላለፍ ዳይሬክተር አቶ ካሳሁን ዘውዴ በጉዳዩ ላይ ምላሽ ሲሰጡ፤ ችግር መኖሩን አምነዋል። ሆኖም ችግሩ የተፈጠረው የቤት ዕድለኞች የደረሳቸውን ሳይትና ብሎክ፣ መቼ እንደሚረከቡ እና ማሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች በተለያዩ የመረጃ ማሰራጫ መንገዶች ኮርፖሬሽኑ አሳውቆ እያለ ተገልጋዮቹ በተያዘው ፕሮግራም ባለመገኘታቸው ነው ብለዋል።

በቀን በአማካኝ አንድ ሺህ 500 ተገልጋዮችን እያስተናገድን ስለሆነ ችግር ሊያጋጥም እንደሚችል የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ ሆኖም ግን ችግሩን ለመፍታት በቂ የሰው ኃይል በማሰማራት እና ግብዓቶችን በማሟላት በማንኛውም ሰዓት አገልግሎት ለመስጠት እየሠሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ፤ 20 ሺህ 310 ቅጽ 09 የወሰዱ ሲሆን የባንክ ክፍያ ማዘዣ የወሰዱት ደግሞ አራት ሺህ 379 ናቸው። ቀሪዎቹ ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚስተናገዱ ይሆናል። ውል የፈጸሙት ሦስት ሺህ 51 ሰዎች ሲሆኑ አገልግሎቱን ለመስጠት ከቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በተጨማሪ ከአዲስ አበባ መሬት ልማት እና ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተወጣጡ 430 ሠራተኞች በጋራ እየሠሩ ነው።

ህጋዊ ውክልና ያላቸውን ባለጉዳዮች መንግስት ባስቀመጠው መመሪያ መሰረት እንደሚስተናገዱ የተናገሩት ዳይሬክተሩ፣ ተጋልጋዩ ከደላላ እና ሌባ ራሱን እንዲጠብቅ እና መንግስት ያቀረበለትን አገልግሎት በተሻለ መልኩ እንዲጠቀም መክረዋል።



አቶ ተክሌ ጆንባ

# ሲዳማ ክልል

## የሌማት ትሩፋት ምርቱን ከአራት እጥፍ በላይ ለማሳደግ አቅዷል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ ፡- በሚቀጥሉት አራት ዓመታት በሌማት ትሩፋት ምርታማነቱን ከአራት እጥፍ በላይ ለማሳደግ እየሰራ መሆኑን የሲዳማ ክልል የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ተክሌ ጆንባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ሶስት ወራትን ያስቆጠረው የሌማት ትሩፋት ስራ በማጠናከር በቀጣዮቹ አራት ዓመታት ውስጥ የእንስሳት ተዋጽኦ ምርትና ምርታማነትን በአራት እጥፍ ለማሳደግ ታቅዶ እየተሰራ ነው።

በሌማት ቱሩፋት በሚቀጥሉት አራት ዓመታት 297 ሚሊዮን 152 ሺህ ሊትር የወተት ምርትን ወደ 5 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሊትር፤ የማር ምርትን ደግሞ ከአንድ ሺህ 341 ቶን ወደ 9 ሺህ ቶን፤ የዶሮ ሥጋ ምርትን ከ1 ሺህ 772 ቶን ወደ 13 ሺህ 327 ቶን ፣ የእንቁላል ምርትን ደግሞ ከ346 ሚሊዮን 636 ሺህ 907 ወደ 3 ነጥብ 2 ቢሊዮን ለማሳደግ ታቅዶ እየተሰራ ነው ሲሉ አቶ ተክሌ ተናግረዋል።

አቶ ተክሌ አክለውም፤ በክልሉ የሌማት ቱሩፋት ስራ ከዞን እስከ ቀበሌ ተግባራዊ ሆኗል። ወጣቶች፣ ሴቶችና አርሶ አደሮችን በማደራጀት በቂ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። በዚህም የወተት፣ የማርና የዶሮ ማርቢያ መንደሮች የመለየትና ወጣቶችን የማደራጀት ስራ ተከናውኗል።

አርሶ አደሮች የሚያመርቱትን ምርት ሳይበላሽ ወደ ገበያ እንዲያቀርቡ ለማስቻል የመሸጫ ቦታዎችን የማመቻቸት ስራ በተቀናጀ መንገድ እየተከናወነ ይገኛል ያሉት አቶ ተክሌ፤ ለአብነትም ከይርጋለም የተቀናጀ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በመስራት የሚያጋጥሙ የገበያ ችግሮች እንዲቀረፉ መደረጉን ጠቁመዋል።

በዶሮ ልማት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ ቢሆንም በክልሉ የአንድ ቀን ጫጩት እጥረት መኖሩን አቶ ተክሌ ገልጸው፣ ችግሩን በክልል አቅም መፍታት ስላልተቻለ የዶሮ ጫጩት አቅርቦቱ ላይ እክል መፈጠሩን አስረድተዋል።

የሌማት ትሩፋት የስነ-ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የወጪ ንግድ ገቢን ለማሳደግ እንዲሁም ከውጭ የሚገባ ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት ያግዛል። በተጨማሪ የስራ እድልን በመፍጠር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል።

የህፃናትን መቀንጨር ለመከላከልና እንደሀገር ያለውን ስርዓተ-ምግብ ጤናማ ለማድረግ የሌማት ትሩፋት ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ በክልል ደረጃ ትኩረት እንደተሰጠው ተናግረዋል። የሌማት ትሩፋት የአራት ዓመት ዕቅዱን ለማሳካት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረት እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።

ዜና

# በሁለተኛው ዙር 107 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ የሰብዓዊ ድጋፍ ቀርቧል

## - ከስምንት ሚሊዮን በላይ ዜጎች ድጋፍ ይፈልጋሉ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በሁለተኛው ዙር 107 ሺህ 592 ሜትሪክ ቶን እህል ሰብዓዊ ድጋፍ ለትግራይ፣ ለአማራና ለአፋር ክልሎች መቅረቡን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ገለጸ።

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ህዝብ ግንኙነት ቢሮ ኃላፊ አቶ ደበበ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሰላም ስምምነቱ ከተፈጸመ በኋላ የሰብዓዊ ድጋፉ አቅርቦቱ ቀጥሏል።

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በግጭት ለተጎዱ የትግራይ፣ አማራና አፋር ክልል ዜጎች የመጀመሪያ ዙር ሰብዓዊ ድጋፍ ከጥቅምት 23 እስከ ታህሳስ 10/ 2015 ዓ.ም ድረስ መሰራጨቱን የገለጹት አቶ ደበበ፤ በሁለተኛ ዙርም ከታህሳስ 11 እስከ ጥር 25/ 2015 ዓመተ ምህረት ድረስ መሰራጨቱን አስረድተዋል። በዚህም 107 ሺህ 592 ሜትሪክ ቶን እህል ሰብዓዊ ድጋፍ ለትግራይ፣ ለአማራና ለአፋር ክልሎች ቀርቧል።

አንድ ሚሊዮን 313 ሺህ 848 ሊትር ነዳጅ በየብስ እንደተላከ በመጠቆም፤ በተጨማሪም ወደ መቀሌና ሽሬ አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር መላክ መቻሉን አብራርተዋል። ሁለተኛው ዙር የሰብዓዊ ድጋፍ 78 በመቶ መቅረቡን አቶ ደበበ ጠቁመዋል።

የሰብዓዊ ድጋፉ በመንግስትና በአጋር አካላት፤ በዓለም ምግብ ፕሮግራም እንዲሁም መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ እያደረገ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ ሰብዓዊ ድጋፍን በማቅረብ የተሳተፉ 29 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መኖራቸውን ጠቅሰዋል። ድርጅቶቹ እየተሳተፉ ያሉት ምግብ፣ አልሚ ምግብ፣ መድኃኒት፣ የመጠለያ ቁሳቁስ፣ የንፅህና መጠበቂያ፣ የትምህርት ቁሳቁና የግብርና ግብዓቶች መሆናቸውን ተናግረዋል።የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ 119 አጋር ድርጅቶች መኖራቸውንም አክለዋል።

በተለይም በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በትግራይ ክልል አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ በሁሉም ዞኖች ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው ያሉት ኃላፊው፤ በተመሳሳይ በአማራ ክልል በተለይ ዋግኽምራ፣ ሰሜን ጎንደርና ሰሜን ወሎ በድምሩ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሕዝብ ሰብዓዊ ድጋፍ እንደሚፈልግ ጠቁመዋል። በአፋር ክልልም 715 ሺህ ሕዝብ ድጋፍ የሚፈልግ መሆኑን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊዋ አስታውቀዋል።

በድምሩ ከስምንት ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ድጋፍ የሚፈልግ ሲሆን፤ የጥቅምት ወር የሰላም ስምምነትን ተከትሎ ያልተገደበ የሰብዓዊ ድጋፍ በመላክ በኩል የመጀመሪያውን ዙር መቶ በመቶ ማሳካት መቻሉን ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ኮሚሽኑ በአጣዬ፣ አጾኪያ፣ ኤፍራታና በደብረ ብርሃን ለተጎዱ ዜጎች የሰብዓዊ ድጋፍ ማድረጉን አቶ ደበበ ገልጸዋል።

# የምሥራቅ አፍሪካ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ድርጅቱ አፍሪካ ቀንድ ላይ የሚኖር የጸጥታ ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባት በሚያስፈልግበት ጊዜ የህግ ከለላ ያለው ኃይል ተልዕኮ የትኛውም አካባቢ ላይ ዘምቶ ጸጥታን የሚያስከብር አካል ያለው ሲሆን፤ በስብሰባውም ይህንን ኃይል በምን መልኩ ማሰማራት፣ ማብቃት፣ ማደራጀት ይኖርበታል የሚለው እንደሚነሳ ጠቁመዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል የቀጣናውን ብሎም የሀገሪቱን ሰላም እና ደህንነት ለማስጠበቅ፣ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችንና ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የሚያስችል አዲስ አደረጃጀት ለማቋቋም ታስቦ ጉባዔው እየተካሄደ እንደሚገኝም አብራርተዋል።

የምስራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል የቀጣናውን ብሎም የሀገሪቱን ሰላም እና ደህንነት ለማስጠበቅ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን እና ሽብርተኝነትን ለመዋጋት የሚያስችል አዲስ አደረጃጀት ለማቋቋም ጉባዔው እየተካሄደ እንደሚገኝ የገለጹት ሜጀር ጄኔራል ተሾመ፤ የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል በቀጣናው ያለውን ተገማች እና ኢተገማች የሰላም እና ጸጥታ ስጋቶችን የበለጠ መከላከል እና መቅረፍ የሚቻልበትን ቁመና መገንባት እንደሆነ አብራርተዋል።

ጉባዔው ድርጅቱ ከአደረጃጀት አንጻር ራሱን እንደገና ለማደራጀት እና የራሱ የደህንነት ምክር ቤት እንዲኖረው የሚያስችል ነው ብለዋል።

ጉባዔው የተቋሙን አቅም እና ችሎታን የሚያሳድጉ እና የሚያጎለብቱ ጥናቶችና የፖሊሲ ማሻሻዎች እንዲደረጉ ውይይት ይደረግባቸዋል ተብሏል። በተጨማሪም ቀደም ሲል ያልነበሩ የዲፕሎማሲ እና የጸጥታ ጉዳዮች ላይም ውይይት ይደረጋል።

ከዚህ ቀደም በነበረው አደረጃጀት የነበረው ወታደራዊ መንገድ ብቻ ነው ያሉት ሜጀር ጄኔራሉ፤ በአዲሱ አደረጃጀት በዲፕሎማሲ መንገድ የሚፈቱ ችግሮችን በዲፕሎማሲ፣ ምክክር የሚያስፈልጋቸውን በምክክር በተጨማሪም ሽምግልና የሚያስፈልጋቸውን በሽምግልና የሚፈቱበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው ብለዋል።

በጉባዔው የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል በቀጣናው ባሉት ጉዳዮች ድርጅቱ በኃላፊነት መስራት እንዲችል እና በምን መልክ ራሱን ማደራጀት እንዳለበት የታቀዱ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ የደረሰበትን በሚቀጥለው የፖሊሲ ኦርጋን ስብሰባ ላይ እንደሚያቀርብ ተገልጿል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## ሀገርን ወደፊት በማሻገሩ ጉዞ የወጣቱ ሚና የላቀ ነው!

ከለውጡ ዘመን ወዲህ መንግስት ሀገራዊ ስብራቶችን ለመጠገን ሰፋፊ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል። በተለያዩ ዘርፎች የፖሊሲ ለውጥ ከማድረግ ጀምሮ ዘርፎችን በአግባቡ በመገምገም በተጠና መንገድ ሪፎርም ተግባራዊ አድርጓል፤ እያደረገም ነው። በዚህም እየተገኘ ያለው ውጤት ተስፋ ሰጪ ሆኗል።

እነዚህ የሪፎርም ስራዎች ሀገር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበረችባቸውን ያለፉት ሁለት ዓመታት ተቋቁማ ማለፍ እንድትችል አድርገዋል፤ በተሞክሮ ደረጃም ካስገኙት ስኬት አንጻርም ለቀጣይ ሀገራዊ ጉዟችን ተስፋ ሰጪ ምልክት መሆን ችለዋል።

ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያመላክቱት የለውጥ መንግስት ከቀደመው የፖለቲካ ስርአት የሚወርሳቸው ችግሮች ለለውጥ ጉዞው ስኬት ትልቅ ፈተና እንደሚሆኑበት ይታመናል፤ እነሱን ለመቅረፍ የሚሄድባቸው ስትራቴጂክ መንገዶች እና መንገዶቹ የሚገዙበት ጠንካራ ዲሲፕሊንም ሊያስመዘግብ ለሚችለው ስኬት ወሳኝ አቅሙ ናቸው።

ከዚህ አልፎ የለውጡ መንግስት ከቀደመው የፖለቲካ ስርአት የሚወርሳቸው ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስብራቶች የሀገራዊ ሰላምና መረጋጋት ቀጣይ ጠንቅ እንዲሆኑ መቆመሪያ ካርድ አድርገው የሚሰሩ/ የሚሰለፉ የፖለቲካ ኃይሎች ካሉ፤ ችግሩ አጠቃላይ የሆነውን ሀገራዊ የለውጥ መነቃቃት የከፋ ፈተና ውስጥ መከተቱ የማይቀር ነው።

ይህ ደግሞ በኛ ተጨባጭ እውነታ የዕለት ተዕለት ክስተት ከሆነ ውሎ አድሯል። እነዚህ ኃይሎች መንግስትን የሚገዳደሩ አጀንዳዎችን በየወቅቱ በመፍጠርና በተሳሳተ ትርክት በሕዝብ ውስጥ በማሰራጨት፤ መንግስት ከጀመረው የለውጥ ጉዞ ለማሰናከል ፤ መላው ህዝብ ለለውጡ የከፈለውን ዋጋ ትርጉም አልባ ለማድረግ ረጅም ርቀት ሄደዋል፤ እየሄዱም ነው።

መንደርና ሰፈርን፤ ቋንቋና ሃይማኖት መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን ከመፍጠር ጀምሮ የሀገርን ህልውና አደጋ ውስጥ የሚከቱ የተለያዩ ሀገራዊ ስብራቶችን ለመፍጠር ተግተዋል ፤ በዚህም ሀገርና ሕዝብን ያስከፈሉት ዋጋ ከፍያለ ነው። የፈጠሩትም ሀገራዊ የልብ ስብራት ገና አላገገመም።

ለዚህም በዲጅታል ሚዲያ ንግድ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎችን ጨምሮ፤ ራሳቸው ሳይነቁ የህዝብ አንቂ ነን በሚል በዘረኝነት መርገም በተያዙ ግለሰቦች እየተደገፉ ሀገራዊ የፖለቲካ መድረኩ፤ የዘመናዊ የፖለቲካ ልምምድ መድረክ እንዳይሆን እያደረጉ ነው።

ህዝባችን ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተግባራዊ ለማድረግ የጓጓለትን በውይይትና በመነጋገር ችግሮችን የመፍታት የፖለቲካ ባህል እንዳይለማመድ፤ በዚህም ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እንዳይሸጋገር ዋነኛ ተግዳሮት ሆነዋል። ለዚህ ደግሞ በሐሰት ዘገባ፣ ግጭትን በመስበክ፤በሴራ ፖለቲካ አደባባይ የሞሉ ፖለቲከኞቻችንን ለአፍታ መታዘብ ፤ የፌስቡክ እና ትዊተር ገጾችን መመልከት በቂ ነው።

ይህ በአንድም ይሁን በሌላ የመንግስትን የለውጥ ጉዞ በመቀልበስ ሕዝባችንን ወደቀደመው የጥፋት የፖለቲካ አዙሪት ለመመለስ የሚደረግ ርብርብ በሀገሪቱ የነበሩ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስብራቶችን በፍጥነት ጠግኖ ወደ ብልጽግና የሚደረገውን ጉዞ በተሻለ ፍጥነት ለማስቀጠል የሚደረገውን ጥረት ፈታኝ አድርጎታል።

የፖለቲካ ገበያ ነጋዴዎች መንግስትን ፋታ በመንሳት፤ ከጀመራቸው የለውጥ ስራዎች ለማደናቀፍ እያደረጉት ያለው ርብርብ መላው ህዝባችንን እያስከፈለ ያለው ሆነ ፤ ወደ ፊት ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ ከፍያለ ነው። ከዚህ አንጻር እያንዳንዱ ዜጋ እነዚህ ኃይሎች በሀገር ህልውና ላይ ሊፈጥሩ የሚችሉትን አደጋ በአግባቡ ሊረዳ ይገባል።

በተለይም ወጣቱ ትውልድ በነዚህ ኃይሎች የተፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ በሚችሉ ሀገራዊ ስብራቶች የመጀመሪያ ተጠቂ በመሆኑ ከስሜታዊነት ወጥቶ በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ ፤ ሀገርና ህዝብን በሚያስቀድም በኃላፊነት መንገድ በማስተዋል ሊንቀሳቀስ ይገባል። እንደ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ከእርሱ የሚጠበቀውም ይሄው ነው።

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# ጭር ሲል የማንወድ ከሆነ፣ የምንወደው ምንድን ነው?

ግርማ መንግሥቴ

እርግጥ ነው ሳቅ ጨዋታ የለመዱ ቦታና ጊዜያት ጭር ሲሉ ማንም አይወድም። መኖሪያ ቤትም ሆነ አካባቢ እንደዛው ነው። ይሁን እንጂ፣ እያወራን ያለነው ከአገርና ሕዝብ አጠቃላይ ደህንነት አኳያ በመሆኑ ከዚህ ጋር የሚጋጭ አይደለም።

ከሁሉም በላይ "ጭር ሲል አልወድም" የሚለው መሰረተ ሃሳብ፣ እድሜ ለድምፃዊት እናና ዱባለ፣ በዜማ ይታወቃል። ድምፃዊቷ "ጭር ሲል አልወድም" ያለችው በመግቢያችን ላይ ካነሳነው ማህባራዊ አውድ አኳያ ነው።

ልዩነታችን እኛ ጉዳዩን እዚህ ያነሳንበት አቢይ ምክንያት ከ"አገርና ሕዝብ ሰላም፣ ፀጥታና ደህንነት . . ." አንፃር መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ሰፊ ልዩነት ነውና ሁለቱንም በየአውዳቸው ማየቱ ፋይዳው ብዙ ስለሆነ ለዛሬ ይህንን የያዝነውን ይዘን እንዝለቅ።

ዛሬ ላይ ሆነን ድሮን ስናስታውሰው በርካታ ልዩነቶች ያሏቸው ሲሆን፣ ከልዩነቶቻቸውም አንዱ ለጋራ ሰላምና ፀጥታ፤ ደህንነትና ለጋራ ማንነት ቅድሚያና ትኩረት መስጠቱ ነው። ከሁሉም፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ በአገርና ሕዝብ ላይ ምንም አይነት ድርድር አለመኖሩ ነው። በቃ፤ ይኸው ነው።

ድሮ፣ ("ድሮ" ስንል በዚሁ ጸሐፊ እድሜ ማለት መሆኑን ልብ ይሏል)፣ በማንም ሰፈርና አካባቢ፤ በየትኛውም ቦታና ስፍራ ... ጭር እንዳይል አይፈለግም። ድሮ፣ በየትኛውም ሁኔታና አኳኋን ውስጥ ሰላም እንጂ ሁከትና ረብሻ ቦታ የላቸውም። አንዱ ለአንዱ ከማሰብ ውጭ፣ እንዲህ እንደ ዛሬው፣ አይን ያወጣ ባላንጣነትና ጠላትነት የለም።

ሁሉም ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነቃና ከመኝታው ሲነሳ "አገራችንን ሰላም አድርግልን" ብሎ ከመፀለይና ፈጣሪውን አመስግኖ ከመማፀን ውጭ ሌላ ነገር የለም። ይህ ደግሞ በሴራውም ሆነ እሬቻው፤ ጨምበላላውም ሆነ ሌላው ያውና ያው ነው። ዛሬስ? ዛሬ "ሁሉም ነገር የተገላቢጦሽ ሆኗል" መባል ከተጀመረ ሰንብቷል። ልክ ሰላም እንደ ራቀን፣ ፍቅር እንደራበን ... ሁሉ የምንወደው በማንወደው ከተተካ ቆይቷል።

ዛሬ፣ በችግር ላይ ችግር እንጂ በፍቅር ላይ ፍቅር ... ተረት የሆነ ሁሉ ይመስላል። ዛሬ፣ ነገሩ ሁሉ "የበላችው ያገሳታል፤ በላይ በላዩ ያጎርሳታል" እንደ ተባለው ነገሮች ሁሉ ከድጡ ወደ ማጡ እየሄዱ እንጂ በተቃራኒው ሲጓዙ አይታዩም። ያኛው ትኩሳት "በረደ" ሲባል ይሄኛው ያገረሽበታል።

እዛጋ እየነደደ ያለው እሳት "ጠፋ" ሲባል እዚህ ጋ ያለው ይለኮስና ይንቦለቦላል፣ ይንቀለቀል ዘንድ ይቆሰቆሳል። እዛ ማዶ ያለው ውሃ "ጠራ" ሲባል እዚህ ያለው ይደፈርሳል። በመሆኑም፣ እምንጠጣው እያጣን ተቸግረናል። ብርሀን በጭለማ እየተተካብን እነሆ ከቀናት ወደ ቀናት፣ ከወራት ወደ ወራት፣ ከአመታት ወደ አመታት ... "እየተሸጋገርን" እንገኛለን።

መሸጋገራችን ባልከፋ፣ ችግሩ ሁሌም "መሸጋገሪያ ..." እየተባለ (ገጣሚው "መለየት አቃተኝ ዳንሱን ከዳንሰኛ" እንዳለው አይነት) የሚሻገረውን ከማይሻገረው፤ የማይሸጋገረውን ከሚሸጋገረው መለየት ማቃቱ እንጂ።

ድሮ፣ "የሰው ጠላት አውሬ ነው" ይባል ነበር ነው የሚባለው። ዘመናትን በድርጊት ቅደም ተከተል የገመገሙ ሊቃውንት አባቶቻችን ዛሬ ነገሩ ሁሉ የተገላቢጦሽ ሆነና "የሰው ጠላት ሰው ነው" ወደ'ሚል አሳዛኝ ተረክ ተቀይሯል ነው የሚሉት።

እዚህ ላይ በምሁራን ዘንድ አብዝቶ የሚጠቀሰውን የእንግሊዙን ፈላስፋ፣ በርትራንድ ራስልን መጥቀስ ይቻላል። በርትራንድ አንዲት እናት በወቅቱ በነበረው ብልሹ አሰራርና አመራር ተበሳጭተው ወደ ጫካ ሲሄዱ ያገኛቸዋል። "ምነው፣ ወዴት ነው?" ሲልም ይጠይቃቸዋል።

ሁሉንም ይነግሩታል። አቅጣጫቸውም ወደ ጫካው መሆኑንም ራስል ይረዳል። "እዛ እኮ አውሬ አለ" ሲልም ይነግራቸዋል። "እዚህ ካለው [ዞ'ለነዋል] እዛ ያለው አውሬ ይሻላል።" ብለውት መንገዳቸውን ቀጠሉ።

እርግጥ ነው፣ እኛ እዛ ደረጃ ደርሰናል/ አልደረስንም ሌላ ነገር ነው። ምናልባትም ያከራክር ይሆናል። ባያከራክር እንኳን ያወያይ ይሆናል። ጉዳያችን እሱ አይደለምና ወደ"ጭር ሲል አልወድም" ርእሰ ጉዳያችን እንሂድ።

አንዳንድ ቆሽታቸው እርርርርር... ድብን.... ያለ ሰዎች ሲናገሩ እንደሚሰማው የዚህ ሁሉ ክፋትና ተከታዮቹ መንስኤ "ጭር ሲል" የማይወዱ ሰዎች እየተበራከቱ መምጣታቸው፤ የንፁህንን ሕይወት አሲዘው የፖለቲካ ቁማር የሚቆምሩቱ እየበዙ መምጣታቸው ነው።

"አንዳንድ" (እቺ "አንዳንድ" በየት በኩል ዞራ መጣች ደግሞ) "የድሮ ናፋቂዎች" እንደሚሉት፣ ድሮ የቅድሚያ ቅድሚያ ሲሰጥ የነበረው ለአብሮነት፣ አብሮ ስለመኖር ነበር። ዛሬ ይህ ተራውን ለ"እኔ"ነት አስረክቦ እብስ ብሏል። የ'ሱ እብስ ማለት ደግሞ የዘመኑን እዳ ከመረው እንጂ ገብስ አላደረገውም።

እነዚሁ "አንዳንድ ... የድሮ ናፋቂዎች" እንደሚሉት "83"ን ተገን አድርጎ ብቅ ያለው "እኔ"ነት፣ ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሯ ትሄዳለች ... እንዲሉ፣ "ድሆ ድሆ ..."፤ በፍጥነት ኢትዮጵያን አጥለቅልቆ ኢትዮጵያዊነትን አደብዝዟል።

ከሁሉም የከፋው መግባቢያ ይሆን ዘንድ ታስቦበት ለሰው ልጅ ብቻ በፈጣሪ የተሰጠው ቋንቋ ሳይቀር እያታኮሰ መገኘቱ፣ አካባቢያዊነት እያጋደለና እያገዳደለ ለ"ጭር ሲል አልወድም" አፍቃሪና አቀንቃኞች ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ ነው። ታዲያ ከዚህ በላይ "ጭር ሲል አልወድም ..." ከወዴት ይገኛል?

ባጠቃላይ፣ ይህ ጽሑፍ ለጥያቄያዊ ርእሳችን፣ "ጭር ሲል የማንወድ ከሆነ፣ የምንወደው ምንድን ነው?" በማለት ለሰየምነው ርእሰ ጉዳያችን ምላሽ ሰጥቶ ይሁን ወይም/እና አይሁን አናውቅም። ምላሽ ሰጠም አልሰጠም ጉዳዩ እሱ ባለ መሆኑ ብዙም አያሳስብም።

የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ለጉዳዩ መልስ የሚሆነው "እያንዳንዳችን ጭር ሲል እንወዳለን፣ ወይስ ሳይል?" ለሚለው "ራስ መዛኝ ጥያቄ" የምንሰጠው መልስ ነውና እሱው ላይ አተኩረን አንዳች አገራዊና ሕዝባዊ ፋይዳ ያለው ውሳኔ ላይ ከደረስን በቂ ነው።

**ቸር እንሰንብት።**

# ነፃ ሃሳብ

# ለዘላቂ ሰላም አዩታዩ ያለ ቁርጠኝነት

በትረ ሙሴ (መልክ ኢትዮጵያ)

የፌዴራል መንግስት እና የሕወሓት የሰላም ስምምነት ኮሚቴ አባላት ለመጀመሪያ ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት አካል በሆነው ‹ሀላላ ኬላ› ምክክር አድርገዋል። በውይይታቸውም በሰላም ስምምነቱ አፈጻጸም ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራትን በመገምገምና በቀጣይ ትኩረት በሚያሻቸው የሁለትዮሽ ጉዳይ ላይ መነጋገር መቻላቸው ተገልጿል።

በዚህ ውይይት ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የሰላም ስምምነት ሂደቱን በተመለከተ ወደትግራይ የሚደረጉ በረራዎች እንዲጨምሩ፣ በባንክ እንቅስቃሴ ዙሪያ ያለው ሂደት እንዲፋጠን፣ ሌሎች የእርስ በርስ መተማመንን የሚጨምሩ እና የዜጎችን አኗኗር ቀላል የሚያደርጉ አገልግሎቶች እንዲፋጠኑ መመሪያ ማስተላለፋቸው በብሔራዊ ደህንነት አማካሪያቸው በኩል መገለጹ ተሰምቷል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተገኙበት የነዚህ ሁለት ቡድን የፊት ለፊት ምክክር ለያዝነው ሀገራዊ እርቅና ሰላም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ብዬ አምናለሁ። ተስፋ ሰጪ እንደሆነ ከተነገረለት ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ወዲህ የመንግስትና ሕወሓት የሰላም ኮሚቴ አባላት በኬንያ ናይሮቢም ተገናኝተው መክረዋል። በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ የተመራ የልዑክ ቡድን መቀሌ ገብቶ ከሕወሓት ቡድን ጋር መክሯል። ከዚህ ሁሉ ሂደት በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት የፊት ለፊት ውይይት አድርገዋል። ይሄ የሚያሳየው በሰላም ስምምነት ሂደቱ ላይ ከሁለቱም ወገን ቁርጠኝነት መኖሩን ነው።

እንደ ሀገር ያሳለፍናቸው ሁለት የጦርነት አመታት ምን እንደነበሩ ማስታወስ አይከብዱም። እንደ ሀገር፤ እንደ ህዝብ ብዙ ነገራችንን አጥተንባቸዋል። ሞትና የአካል ጉዳቱን፣ ስቃይና እንግልቱን፣ ረሃብና ስደቱን ደርሶብናል። በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው፣ በማህበራዊ ሕይወታችን ይሄ ነው የማይባል ስብራት ደርሶብናል። አሁን ላይ እያሰቃየን ያለው የኑሮ ውድነት እንኳን በዚህ ጦርነት ተምጦ የተወለደ ነው፡፡

የተፈረመውን የሰላም ስምምነት ሂደት ተግባራዊ ለማድረግ ገና የሚቀሩ ሂደቶች እንዳሉ ይታወቃል። አሁን ባለው ሂደት ግን ሀገራችን ተስፋ ሰጪ በሆነ አስተማማኝ ሰላም ውስጥ መሆኗን መናገር ይቻላል። የቀሩት የስምምነት ሂደቶች ወደ መሬት ወርደው ተፈጻሚ ሲሆኑ ደግሞ ከዚህ በተሻለ ሰላም ውስጥ እንደምንቆም እምነት አለን። እንደ ሀገር እንደ ህዝብ የምንፈልገውን አስተማማኝ ሰላም ለማምጣት ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው እርሱም የሰላም ስምምነት ሂደቱ ተግባራዊ እንዲሆን የበኩላችንን መወጣት ነው፡፡

የህዝብ ሰላም ያለው በሁለቱ ሀይሎች መተማመን ውስጥ ነው። የሀገር ሰላም ያለው በሰላም ስምምነት ሂደቱ ውስጥ ነው። ይሄ የሰላም ስምምነት ሂደት እንዲቀላጠፍ ሁለቱም ሀይሎች እኩል ሀላፊነት እንዳላቸውና ለትግበራውም ሀገርና ህዝብን ባስቀደመ መልኩ ይሁንታን ማሳየታቸው የሚበረታታ ነው።

የዚህ ዓለም ምርጡ ጀግንነት በሰላም ውስጥ ማሸነፍ ነው። በመግደልና በመሞት ውስጥ ያለው ጀግንነት ጊዜ ያለፈበት ጀግንነት ነው። የዚህ ዓለም የከፋው ጀግንነት ደግሞ በሀገራችን እየሆነ እንዳለው በወንድማማቾች መካከል የሚፈጠር የብኩርና ጀግንነት ነው። ወንድሙን ገሎ ጀግና የተባለ ባለኒሻን ዓለም የላትም። አይደለም ወንድምን ጠላትን መግደል እንኳን በዚህ ዘመን ጀግና አያስብልም፡፡

ጀግንነት ሰላም ውስጥ ብቻ ነው ያለው። ጀግንነት ጥላቻን በፍቅር በመሻር ውስጥ ነው ያለው። እነጋንዲ፣ እነማንዴላ ዓለም መቼም የማትረሳቸው የሰላም ጀግኖች ናቸው። እነ ቼኮቬራ፣ እነማዘር ተሬዛ ዓለም ዳግም እንዲፈጠሩ የምትመኛቸው የሰው ልጅ ሁሉ ጠባቂዎች ነበሩ። ኢትዮጵያ የሰላም ጀግና የላትም። ሀገሬ የፍቅር አርበኛ የላትም። የእኛ ሀገር ጀግኖች በጦርነት ውስጥ የተፈጠሩ ናቸው፡፡

የእኛ ሀገር ጀግኖች በመግደልና በመሞት ውስጥ የቆሙ ናቸው። ጀግና በሰላም ውስጥና በጦርነት ውስጥ ሲፈጠር ሁለት አይነት ነው። የሰላም ጀግና ሞትን የሚጸየፍ፣ ጦርነትን የሚጠላ ነው። የሰላም ጀግና ጥላቻን የሚሽር፣ ሰውነትን የሚሰብክ ነው። የጦርነት ጀግና ግን በመግደል የሚደሰት፣ በመሞት የሚኮራ ነው። በማስጨነቅና በመጨነቅ የሚደሰት እንዲገድልና እንዲሞት ምክንያት የሚሻ ነው፡፡

አሁን ላለችው ጎስቋላ ሀገራችን የሚበጃት በሰላም ውስጥ የበቀለ ጀግና ነው። አሁን ላለው ድሀ ህዝብ የሚበጀው እንደ ሙሴ ከባርነት የሚያወጣው የሰላም አለቃ ነው። እንደ ኤልሳ የመከራውን ባህር የሚያሻግር፣ የጉስቁልናውን መንገድ የሚከፍል የፍቅር አርበኛ ነው። እንደ ሀገር የሰላም ጀግና ርቦናል። ጦርነትን ሽሮ ሰላም የሚሰብክ፣ ፍቅር የሚያስተምር ጳውሎስን እንሻለን።

በሎጥ እኔነት ውስጥ ‹እኛ ወንድማማቾች ነን› መለያየትም ሆነ መጠላላት አያስፈልገንም እንዳለው አብረሃም የፍቅር ሰው እንሻለን። በጦርነት ማሸነፍ ሳይሆን በሰላም ውስጥ ማሸነፍ ነው ሀገራችንን ከኋላ ቀርነት የሚታደጋት። ጀግንነት ካማረን ከውጭ ጠላቶቻችን ጋር ይሁን። ዓድዋ ዛሬም ድረስ በኩራት የሚነሳው ጀግኖቻችን በጠላት ላይ ስለተነሱ ነው።

ዛሬም ድረስ እንደ አዲስ የሚወሳው በአንድነትና በህብረት የማይቻል የሚመስልን እውነት ስለቻልን ነው። ኢትዮጵያዊነት በአንድነት ተነስተን በጋራ ስንቆም እንደ ዓድዋ ነን። በጠላቶቻችን ላይ ጀግና መሆን እንችላለን። ተለያይተን ስንቆም ግን ገድለንና ሞተን ነውር የሞላው የብቻ ታሪክ ከመጻፍ ባለፈ አንጀግንም፡፡

አንዳንድ ጊዜ ለሀገራችን ስንል የምንከፍለው መስዋዕት አለ። አንዳንድ ጊዜ ለድሀ ህዝባችን ስንል የምንተወው ነገር አለ። አንዳንድ ጊዜ ለተስፈኛው ትውልድ ስንል በይቅርታ የምንሻገረው ስህተት ይኖራል። ሀገራችን ውስጥ የተፈጠሩ ጦርነቶች፣ ተፈጥረውም ብዙ ዋጋ ያስከፈሉን ነውጦች ትንሽ ባለማሰብ፣ ትንሽ ባለመታገስ የሆኑ ናቸው፡፡

ዛሬ ላይ ብዙ ዋጋ የከፈልንባቸው የእርስ በርስ ጥላቻዎች ተቀምጦ ባለመነጋገር እና የሰላምን ዋጋ ካለመረዳት የመጡ ናቸው። ይሄን የሚሽር ፖለቲካዊ እርምጃ ያስፈልገናል። ይሄን የሚሽር የሀሳብ ልዕልና ያስፈልገናል። ከመግደልና ከመሞት ወጥተን ጀግና የምንሆንበትን የሰላም መንገድ መፈልግ አሁን ላለችው ኢትዮጵያ ምርጡና አስተማማኙ የእድገት መንገድ ነው። አዎ..አሁን የቀረን አስተማማኙ መንገድ በሰላም ውስጥ ጀግና መሆን ብቻ ነው። አሁን የቀረን አዋጩ መንገድ ተነጋግሮ በመግባባት ችግሮችን መፍታት ብቻ ነው፡፡

ዓለም የሌለው የእኛ የሆኑ አንዳንድ ነውሮች አሉን። ቢፈለጉ ከእኛ ውጭ የትም የማይገኙ አንዳንድ የጦርነትና የጥላቻ እውቀቶች አሉን። በእኛው ተፈጥረው፣ በእኛው በልጽገው እኛኑ የበሉና እየበሉ ያሉ የጦርነት ታሪኮቻችን ብዙ ናቸው። ሰው በጦርነት ባለታሪክ ሊሆን አይችልም። ሀገር ገደሎ በመሞት ውስጥ ስልጣኔዋን ማረጋገጥ አትችልም። ታሪክ ያለው ድህነትን በማሸነፍ ውስጥ ነው፡፡

ጀብድ ያለው ኋላቀርነትን በመርታት ውስጥ ነው። እንደ ሀገር መቀጠል ካማረን ከጦርነት አስተሳሰብ ወጥተን ፍሬ ወዳለው የእድገትና የስልጣኔ እሳቤ መመልከት አለብን። እንደ ህዝብ ታሪካችን እንዲታደስ ሀይል ለበስ ከሆኑ ነውረኛ እውቀቶች ርቀን እርቅና ምክክርን ወዳስቀደሙ የመፍትሄ አቅጣጫዎች መማተር አለብን። ይሄ የአዲሷ ኢትዮጵያ አዲስ እውቀት ነው። ይሄ የነበሩ፣ ያሉና የሚኖሩ ሀገራዊ ችግሮቻችንን የሚቀርፍ የአዲስ ፖለቲካ ተራማጅ ስርአት ነው፡፡

**ጀብድ ያለው ኋላቀርነትን በመርታት ውስጥ ነው። እንደ ሀገር መቀጠል ካማረን ከጦርነት አስተሳሰብ ወጥተን ፍሬ ወዳለው የእድገትና የስልጣኔ እሳቤ መመልከት አለብን። እንደ ህዝብ ታሪካችን እንዲታደስ ሀይል ለበስ ከሆኑ ነውረኛ እውቀቶች ርቀን እርቅና ምክክርን ወዳስቀደሙ የመፍትሄ አቅጣጫዎች መማተር አለብን**

ከዚህ በኋላ የምንመለስበት ትላንት የለም። ከዚህ በኋላ የምንመለስበት የጦርነት ታሪክ ሊኖረን አይገባም። ሀገራችን በብዙ ቆስላለች፣ ህዝባችን በብዙ ደክሟል። ትውልዱ የጦርነት ታሪክ፣ የጥላቻ ተረት መስማት ሰልችቶታል። ጆሮዎቻችን ስለ ሞት መስማት ሰልችቷቸዋል፣ አይኖቻችን የወገንን ስቃይ ማየት ታክቷቸዋል። እስኪ ሌላ እንሁን… እስኪ በመነጋገር መግባባትን፣ በመነጋገር ሀገር መፍጠርን የእውቀታችን መጀመሪያ እናድርገው፡፡

እስኪ ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት የፖለቲካችንና የፖለቲከኞቻችን ቀዳማይ መርህ ይሁን። ኮሽ ባለ ቁጥር ውረድ እንውረድ ይብቃን። እኔ ያልኩት ከሌላው ጋር አልገጥም ሲል ያን ልዩነት በምክክር መፍታት የቀጣይ እቅዳችን ቁልፍ ሚና ይሁን። በዚህ እውነት ውስጥ ነው አልወለድ ያለችውን ሀገራችንን ልንወልዳት የምንችለው። በዚህ መርህ ውስጥ ነው መምጫዋ የራቀንን ኢትዮጵያ ወልደን የምንስማት፡፡

እንደ መንግስት ሀገር ለማሳደግ እቅድ እናወጣለን። እንደ ግለሰብ ሕይወታችንን ለመቀየር በማሰብ እንጓዛለን። የአመት፣ የሁለት አመት እያልን እቅድና እስትራቴጂ እንነድፋለን። የአጭር ጊዜ፣ የረጅም ጊዜ እያልን በህዝብ ተወካዮች ፊት የጋራ አቅጣጫ እናስቀምጣለን። እኚህ ሁሉ ሀገራዊና ግለሰባዊ እቅዶቻችን የሚሰምሩት በሰላም በኩል ሲያልፉ እንደሆነ ግን ገና አልገባንም።

ሰላም አጥተን ገንብተን የፈረሱብን፣ ክበን የተናዱብን ጉዳዮቻችን ብዙ ናቸው። መንግስት እንኳን በሁለት አመቱ ጦርነት እጅግ በርካታ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ አየር ማረፊያዎችን፣ መንገዶችን ሌሎችንም ብዙ ክበን የተናዱብንን ማህበራዊ መገልገያዎችን በመገንባት ላይ ነው። እቅድ ስናወጣ ሰላምን አጀንዳችን ማድረግ እንዴት አቃተን? ሰላም በሌለበት የሚመጣ ተስፋም ሆነ ብርሃን እንደሌለ እንዴት ጠፉን? እቅዶቻችን ያልሰመሩት፣ ሀገራዊ መሻታችን ያልተሳኩት በእቅዳችን ውስጥ ሰላም ስለሌለ ነው። በእቅዳችን ውስጥ ሰላምና ፍቅር፣ እርቅና ምክክር ሲኖሩ ነው ዘርተን የምንቅመው ወልደን የምንስመው፡፡

ጽንፈኝነትን የሚገል፣ እኔን የሚሽ የሰላም እቅድ ያስፈልገናል። ጦርነትን የሚጸየፍ፣ ጥላቻን የሚንቅ የፍቅር ሀሳብ ግድ ይለናል። ለጀመርነው የሰላም እርምጃ፣ ለጀመርነው የእድገት ራዕይ ጦርነትን ታሪክ ያደረገች ሀገር ታስፈልገናለች። በሰላም ማሸነፍን መልመድ አለብን። ተነጋግሮ በመግባባት ወንድማማችነትን ማስቀጠል እንደሚቻል ማወቅ አለብን።

ተጣልተን መታረቅ ይብቃን። ተገዳድለን መጨባበጥ ይብቃን። ከመጣላታችን በፊት፣ ከመገዳደላችን በፊት መግባባትን እንማር። ፖለቲከኞቻችን የፖለቲካ ጽንሰ ሀሳብ ሊገባቸው ይገባል። ነገ ላይ ትውልድ ገልጦ የሚያነበውን የጥላቻ ታሪክ መጻፍ ሌላ ጥላቻን ከመፍጠር ባለፈ አይጠቅመንም። በሰላም ውስጥ ጀግና መሆን እንደሚቻል የተረዳ ትውልድ ነው የሚያስፈልገን።

በወንድማማቾች መካከል የሚፈጠር ጥል፣ የሚፈጠር አተካራ ሀገር ከማበላሸት ባለፈ ትርፍ እንደሌለው የተረዳ ማህበረሰብ ነው የሚያስፈልገን። በወንድማማቾች መካከል የሚፈጠር የእልሸኝነት ጀብድ ነገ ላይ ምነው ባላደረኩት እንድንል ከማድረግ ባለፈ የሚያመጣልን ልዕልና የለም፡፡

የሁለት አመቱን ጦርነት መለስ ብለን ብናስተውለው ከዚህ እውነት የራቀ ሆኖ አናገኘውም። እነዚያ የሞቱ ነፍሶች፣ እነዚያ በማያውቁትና ባልገባቸው ፖለቲካ የተጎሳቆሉ ህጻናት፣ እነዚያ በረሃብና በስደት የተንገላቱ አዛውንቶች እኛ በፈጠርነው እልሸኝነት የተሰው ናቸው። በሀገር ላይ የተፈጠሩ የኢኮኖሚ ድቀቶች፣ በትውልድ ላይ የተፈጠሩ ስብራቶች፣ በማህበረሰቡ ላይ የተፈጠሩ ጫናዎች በገዛ እጃችን የመጡ ናቸው፡፡

ጀግኖቿን በሰላም ውስጥ የተዋወቀች ሀገር ታስፈልገናለች። ልዩነታችንን በመነጋገር እያጠበብን፣ አንድነታችንን በመመካከር እያጎለበትን ሰላማዊ ሀገር መፍጠር ነው የሚያወጣን። በጦርነት ያለቀስነውን ያክል የምንስቅበት፣ የተጎዳነውን ያክል የምንሸርበት የእርቅና የተግባቦት ጊዜ እንደሚሆን አምናለሁ። ሕወሓትና የፌዴራል መንግስት በሰላም ስምምነቱ ሂደት መሰረት ቀጣይ ሂደቶችን በመከወን ሌላ ተጨማሪ የሰላም ጉልበት እንደሚፈጥሩ በማመን ላብቃ፡፡

# የ480 ዓመት እድሜ ባለጸጋው - ሀላላ ኬላ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ውስጥ የተካተተው የኮይሻ የተቀናጀ ፕሮጀክት፣ ለዳውሮ ሕዝብ አዲስ ዕድልና ተስፋን የሰነቀለት ይመስላል። ለአካባቢው ማኅበረሰብም የማታ ስንቅ እንደቋጠረለት ይታያል። ምክንያቱም በዚህ ፕሮጀክት ሰበብ ዳውሮ ለዘመናት በጉያዋ ደብቃ ይዛ የቆየቻቸውን ሃብቶች ለዓለም ሕዝብ የማሳየት ዕድል ትጎናጸፋለች። የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የቱሪዝም መስሕቦቿን ሸጣ ትልቅ የገቢ ምንጭ ታገኛለች። ዜጎቿም በሥራ እድል እንዳይሰቃዩ ታደርጋለች። እንዴት ከተባለ መልሱ ቀላል ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተደጋጋሚ ቦታውን ጎብኝተውት ከአካባቢው ማኅበረሰብ አልፎ ለሀገር የሚተርፍ ብዙ ሀብት አይተዋልና ታላቁን ሀገራዊ ፕሮጀክት እዚያ ላይ እንዲሠራ ወስነዋል። ከዚህም በላይ ብዙዎች በቴሌቪዥን መስኮት አይተው የዳውሮን ምድር ለመርገጥ እንዲመኟት አስችለዋል።

ምድራዊ ገነት መሆኗንና እምቅ ሀብት እንዳላት አስጎብኝተዋል። እኛም ከሰሞኑ እርሳቸው ረግጠውት የተለያዩ ተግባራትን ሲከውኑበት ያየነውንና የተደመምንበትን ሰው ሠራሽ ሀብት ጀባ ልንላችሁ ወደድን። ይህም የ‹‹ሀላላ ኬላ›› እየተባለ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚጠራው ቅርስ ነው። ለመሆኑ “ሀላላ ኬላ ምንድን ነው? በማን ተሠራ? ለሕዝቡስ ምን ነበር? ለዛሬው ትውልድስ ምን ሰጠ? ካላችሁ በዛሬው ‹‹የሀገርኛ›› መጣጥፋችን እንነገራችሁ ተከተሉን።

ከስሙ አመጣጥ ስንነሳ ‹‹ ሃላላ›› የዳውሮ ንጉሥ መጠሪያ ስም ነው። ‹‹ኬላ›› የሚለው ደግሞ የድንጋይ ካብ (የመከላከያ ካብ) የሚል ትርጉም አለው። ካቡ ባለው ሰባት ረድፍ 1225 ኪሎሜትር የሚሸፍን ሲሆን፤ ለግንባታ 350 ዓመታት ያህል ጊዜን ወስዷል። ከ15 እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ዳውሮን ያስተዳድሩ የነበሩ 14 ነገሥታት የተፈራረቁበትና በቅብብሎሽ የገነቡትም ነው። የሦስት ትውልድ አሻራ ያረፈበትም ነው። እናም 14ኛው ንጉስ ካዎ ሀላላ ነበሩና ኬላውን ማስጨረስ ችለዋል። ይህንን እንዲያደርጉ ያስቻላቸው ደግሞ የካቡ መሠረት ሲጣል ጀምሮ ለመጠናቀቁ ዋስትና የሚሆናቸውን ነገሮችን ነገሥታቱ በማስቀመጣቸው ነው። ይህም ቃለ መሐላ ሲሆን፤ እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ የተሳሰሩበት ነው። ሰባተኛው ትውልድ ላይ የነገሰው “ካዎ ሀላላ”ም ይህንን አድርጓል። የአባቶቻቸውን ስም ይዘው ቅርሱን አስቀምጧል።

ይህ ካብ(ኬላ) የዳውሮ ማኅበረሰብ የብሔሩ ማንነት የተገለጠበት፣ የትውልድ ቅብብሎሽ የታየበት ብቻ ሳይሆን ድንጋይን በድንጋይ ላይ በማነባበር ግዙፍ አለቶችን እያይዞ ዓመታት ያሻገረ ነው። ከሁሉም የሚደንቀው ደግሞ የመንግሥታትን ቅብብሎሽ የሚታይበት መሆኑ ነው።

ይህ ታሪካዊውና ጥንታዊው የኪነ ሕንጻ ግንባታ የዳውሮ ሕዝብ ጥበባዊነቱን ብቻ ሳይሆን ሀገር በቀል እውቀቱን ያሳየበት ነው። ለዚህም ማሳያው አንዱን ረድፍ ጭምር በምን ያህል ርዝመት መሥራት እንዳለበት ተጠቦበታል። እናም አንዱ ረድፍ 175 ኪሎ ሜትር ርዝማኔ ኖሮት እንዲሠራ ነው ያስቻለው። ውፍረቱ ደግሞ ከ2 ነጥብ 5 እስከ 5 ሜትር ይደርሳል። ቁመቱም እንዲሁ ልኬት አለው። ይህም በአማካይ ከ2 ነጥብ 5 እስከ 3 ነጥብ 8 ሜትር ይረዝማል።

“ሀላላ ኬላ” ለምን ዓላማ ተገነባ ከተባለ የታሪክ ባለሙያውና በካቡ ዙሪያ ትናንትና ምርምር ያደረገው ዶክተር አድማሱ አበበ ከዳውሮ ቲዩብ ጋር በነበረው ቆይታ እንዳስቀመጠው፤ ዳውሮዎች ዳር ድንበራቸውን ለማስጠበቅና የመሬት መንሸራተት ለማስቀረት ብለው የገነቡት ነው። የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ በጣም ስለሚያሳስባቸው ጠላትን ከመመከቱ ባሻገር ሌላም ሀገራዊ ጠቀሜታ እንዲኖረው አድርገው ገንብተውታል።

የ480 ዓመት የእድሜ ባለጸጋ እንደሆነ የሚነገርለት ይህ ካብ፤ አገነባቡ አንዳች ዘመናዊ መሣሪያዎችን ሳይጠቀሙ ነው። ሲሚንቶና አርማታም አላስገቡበትም። የሀገር በቀል እውቀት ቴክኖሎጂያቸውን ብቻ ተጠቅመው ነው ዘመንን ያሻገሩት። ስለዚህ የሥልጣኔ ሁኔታቸው ምን ድረስ እንደሚዘልቅ ለዛሬ የግንባታ ባለሙያዎች በደንብ የሚያስተምር ነው።

ስለሥነ-ሕንፃ ጥንታዊነቱ ስናወራም በሰባት የጦር በሮች (ኬላዎች) ከፋፍሎ ዘመናትን ያስተሳሰረም እንደሆነ ይነገርለታል። እነዚህ በሮችም በስተምስራቅ በወላይታ ዞን በኩል ሎማ ወረዳ የዚማ ዋሩማ ዳርሚሳ በር (ሚጻ)፣ በስተደቡብ በጎፋ ዞን በኩል ዲሣ ወረዳ የሾታ ማልዶ ካረ ሚጣ እና በየሊ በር /ሚፃ/፣ በኦሮሚያ ጅማ ዞን በኩል ታርጫ ዙሪያ ወረዳ የአባ ኬላ በር /ሚፃ/፣ በሀዲያና ከንባታ ጠንባሮ ዞን በኩል ገና ወረዳ የዳራ በር /ሚፃ/ በወላይታ ዞን በኩል በዛጋዞ ወረዳ ጋራዳ በር /ሚፃ/ እና የዛባ በር / ሚፃ/ እንዲሁም በኮንታ ልዩ ወረዳ በኩል ቃሎ በር /ሚፃ/ ተብሎ በአድራሻዎች ይጠበቃል፡፡

ኬላው የጠላት ጦር ጥበቃ መከላከያን በምን አይነት መልኩ ማስቀመጥ እንደሚቻልም በሚገባ ያሳየ ነው ይባልለታል። የዳውሮ ሕዝብ በጀግንነት የራሱን ዳር ድንበር ከጠላት ወረራና ጥቃት መከላከል እንዴት እንደሚችል ያረጋገጠ ነውና ሕዝቡ ሉዓላዊነቱን ለማስጠበቅ ምን ያህል ዋጋ እንደከፈለ አሳይቶለታል። በቂ ባይሆንም በሀላላው መኖር እስከ ዛሬ ድረስ ያለው ትውልድ ካቡን ይንከባከበዋል፣ ይጎበኘዋል፣ ለጥናታዊና ምርምር ሥራ ተመራማሪዎች እንዲጠቀሙበት ይደረጋል። የዛሬው ትውልድ የአባቶቻችን የጀግንነት አሻራ ያደንቅበታልም።

ከዚያም አለፍ ሲል አልምተው ለቱሪስት መዳረሻ ያደርጉታል። ከዘርፉ አያሌ የሥራ ዕድል ለመፍጠርም ይጠቀሙበታል። የሕዝብ ተጠቃሚነትንም ያረጋግጡበታል። ከሁሉም በላይ ደግሞ አሁን የመጣውን እድል በአግባቡ ከተጠቀሙና እድሉን ከአሰፉት ለሀገር መልካም ገጽታ ግንባታ ድርሻው ከፍተኛ ነው። ኬላውን በዚህ ባሕሪው ብዙዎች ከቻይናው ‹‹ግሬት ዎል›› እና ከፐርሺያው ‹‹ባቢሎን›› ጋር ያመሳስሉታል። አፍሪካ ውስጥ መኖሩ ደግሞ ለብዙ አጥኚዎች መሠረት እንደሚሆን ይተነብዩለታል። ያው የሚጠቀመው ካለ።

ንጉሥ ሀላላ የድንጋይ ካብ በሰባቱ በሮች በጎጆብና በኦሞ ወንዝ ተከብቦ ያለ አከባቢ ነው። በዚህም በወንዞቹ ኅብረተሰቡ የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ፤ የገበያ ልውውጦችን ከአጎራባች ዞኖች ጋር እንዲያደርጉና ጠንካራ ግንኙነትን እንዲያዳብሩ አስችሏቸዋል። አርቀው በማሰብ ጥቃቶችን በመተንበይ በአንዳንድ ጉዳዮች አለመግባባት ከተከሰተ ተንኳሾች እንዳያገኟቸው ተከላክለውበታልም። የጦረኞች ፈረስ የማይወጣው ድንጋይ ካብ በማስገንባት ከእነዚህ መውጫና መግቢያ በሮች ከጎሳዎች ሹመት በመስጠት ያስጠበቁበትም ነው -ሀላላ ኬላ።

“የድንጋይ ካብ የጠላት መግቢያና መውጫ እንደሚሆኑ በሚገመቱ አካካባቢዎች የጦር በሮች (tooraa miis’aa) በማዘጋጀት በእያንዳንዱ የጦር በር ጠባቂ ሹም (miis’aa iraasha) ሹመት በመስጠት፣ የግዛት ወሰንና የሕዝብ ደህንነትን ያስጠብቁበታልም” ይላሉ የታሪክ ባለሙያው ዶክተር አድማሱ።

የካዎ ሃላላ ድንጋ ካብ (ኬላ) (kawo halaalaa keelaa) መገኛ አሁን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በዳውሮ ዞን ኦሞ ወንዝን ተከትሎ ነው። ኢሳሩ፣ ዲሳ፣ ሎማ፣ ዛባ ጋዞ፣ ጌና፣ ታርጫ ከተማ አስተዳደርና ታርጫ ዙሪያ ወረዳዎችን ያካልላል። ከጋሞ ጎፋ፣ ከወላይታ፣ ከምባታና ጠንባሮ፣ ከጅማ ዞን እና ኮንታ ልዩ ወረዳ ጋርም ይዋሰናል።

ይህ ኬላ ይህንን ሁሉ ዓመት ሲያስቆጥር ዝም ብሎ የተጓዘ አይደለም። ታሪካዊ ነገሮችን እያስቀመጠ፤ የማኅበረሰቡን የሥራ ድርሻ እያሳየና ጥበባዊ እውቀቶችን እያስቀመጠ ነው። በዚህም ግንባታው ሲጠናቀቅ መሠረታዊ ነገሮችን እንዲያስተላልፍ ሆኗል። ለአብነት በየወቅቱ ሲያስተዳድሩት የነበሩትን ነገሥታት ይነግረናል፤ ግዛት ላይ የነበረውን አመራር ያስረዳናል። በተመሳሳይ የትውልድ ቅብብሎሽን ጥቅም ያሳየናል። ምክንያቱም ካቡ ሲገነባ ዓላማው የውጭ ወራሪ ኃይል ወደ ዳውሮ ግዛት ገብቶ የዳውሮን ሕዝብ እንዳይረብሽ ለማድረግና ማዕከላዊ መንግሥቱን ለመከላከል ተብሎ ነው።

የሀላላ ኬላ የተደበቁ ባሕሎችና ማንነቶች የሚታይበት ዶሴ ነው። የትውልዱን ተስፋ የሚያለመልም ምንጭም ነው። ምክንያቱም ይህ ካብ የድንጋይ ካብን ታሪካዊ አመጣጥ የሚያሳይ በመሆኑ በሐምሌ 2000 ዓ.ም በብሔራዊ ቅርስነት ተመዝግቧል። ሀላላ ኬላ የድንበር አጠባበቅ ሥርዓቱ በዚያ ወቅት ምን ይመስላል? የሚለውን የሚተነትኑት ዶክተር አድማሱ፤ ኬላው ዝም ብለው ሲያዩት ጫካ ይመስላል። ወደ ውስጥ ሲገባ ግን እንደ ሀገር መከላከያ በተጠንቀቅ የቆመ ሀገራዊ ስሪት ነው። ለአብነት ከዲዛይን ሥራው ብንነሳ ተፈጥሮን መነሻ ያደርጋል።

የጥርስ አይነት መልክ ያለው ነው። በዲዛይን ሥራቸው የተመጣጠነ ክብደት እንዴት ማምጣት ይቻላል በሚል አስበው ገባወጣ ቢያደርጉትም እንደመንጋጋ ጥርስ በሁለት ረድፍ ደርዝ ይዞ ንቅንቅ የማይል አለት አድርገውታል። ይህንን በማድረጋቸው ደግሞ ማኅበረሰቡን ጎርፍ እንዳይጎዳው አስችለውበታል። ምክንያቱም ኬላውን ከመሠረቱ ጀምሮ ሲገነቡት መሬት ነክቶ እንዲነሳ አድርገው ነው። በቀላሉ ግምቡን ንዶ ውሃ እንዳይገባ አንጸውታል።

ዛሬ ታሪኩን የዳውሮ ሕዝብ ሁሉ ያውቃል። ለዚህ ደግሞ ቀደምት ትውልዶች በግንባታው ሥራ ውስጥ መሳተፋቸውና ከትውልድ ወደ ትውልድም በቃል ሲተላለፍ መኖሩ ሁሉም ታሪኩን በቀላሉ እንዲረዳው እንዳደረገው ተመራማሪው ያስረዳሉ። በተለይም በካዎ ሀላላ አስተዳደር ጊዜ በቤት ውስጥ ያለ ወንድ ትልቅ ኃላፊነት ነበረበት። አንድ ወንድ ልጅ ወክሎ ማሠራት ግዴታ ነው። ወንድ ልጅ ከሌለ ደግሞ አባወራው የቤቱን ሥራ ጭምር በመተው መሳተፍ እንዳለበት ተወስኗል። በዚህም ቅድሚያ ለራሴ ሳይል ኃላፊነቱን ተወጥቷል። በዚህ ግንባታ አባት የሚያርፈው ወንድ ልጅ ሲተካ ብቻ እንደሆነም ይነገራል። ስለዚህ የዳውሮ ማኅበረሰብ ለዚህ የጥበብ ሥራ እጅግ ውድ ዋጋ ከፍሎበታል።

ሌላው ከሀላላ ኬላ ጋር ተያይዞ የምናነሳው ነገር በወቅቱ የነበሩት አባቶች ካቡን እንዴት እንደሠሩት የሚነሳበት ነው። ወታደራዊ ጥበብን ተጠቅመው እንደከወኑት ዶክተሩ ማስረጃ ጭምር በማንሳት ያብራራሉ። የቀን የግንባታ ውሏቸው ሲያበቃ ዝም ብለው ተነስተው አይሄዱም። የቦታውን አቀማመጥና የቆመበትን መንገድ አረጋግጠው ነው። በዚህም ብዙ ጊዜ የቀኑ ሥራቸው የሚጠናቀቀው ተራራን ተገን አድርጎ ነው። ምክንያቱም በእነርሱ እምነት ተራራ አንዱ መከላከያ ነው። በተጨማሪም ውሃ፣ ገደልና መሰል መሰናክሎች ሲያጋጥሟቸው ካቡን ወደ አንድ ሰብሰብ አድርገው ይገነቡታል። ይህ ደግሞ ሰባቱን የጦር በሮች እንዲከፍቱ ያስቻላቸው ነው። ካቡ የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት በመሆኑም በተለይ ለፈረሰኛ ጦር ምሽግነት እንዲያገለግልም ተደርጎ የተሠራ ነው፡፡

የዚህ ታላቅ ታሪካዊ ኬላ አጠናቃቂ ንጉስ ሀላላ ታሪክ አውራሽ ብቻ አይደሉም። ሥልጣንን በግል ጠቅልሎ ከመያዝ ልማድ በመውጣት አዳዲስ የአመራር ስልቶችን ማሳየት የቻሉ መሪ ናቸው። በተለይም ሥልጣንን ለሕዝብ በማካፈልና በየደረጃው በማውረድ ሕዝባዊ አገዛዝን መመሥረቱ ላይ የተዋጣላቸው እንደሆኑ ይነገርላቸዋል። የሕዝብ አንድነትን ከምንም በላይ የሚፈልጉና ዋጋ የሚሰጡም ስለመሆናቸው የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። የታሪክ ቅርሶቹም ቢሆኑ ምስክሮች ናቸው።

ድንጋይ በድንጋይ ላይ በማነባበር ግዙፍ አለቶችን አገናኝተው ታሪክ ያኖሩልንን አባቶች እኛ ማስታወስ የምንችለው ታሪኩንና ጥቅሙን ተረድተን ወደ ልማት ስንቀይረው ነው። ለዚህ ደግሞ ብዙ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረውልናል። አንዱ ታሪካዊዎቹ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ፤ ኮይሻ ለዚህ ትልቁና ቅርቡ ፕሮጀክት ማድረግ አንዱ ነው። እናም እርሱን ከዳር በማድረስ ከዚያ የሚገኘውን ገጸበረከት ለእነዚህ ሀብቶቻችን እንዲተርፍ ማስቻል የዳዎሮ ሕዝብ ድርሻ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሀገር ወዳድ እንደሆነ ማመን ይገባል።

ይህንን ታላቅ ቅርስ ቀደምት የዳውሮ ነገሥታት ጥለውት ያለፉት ዝምብሎ እንዲቀመጥና ዘመናትን እንዲያስቆጥር አይደለም። ቅርሱ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሰው እንዲጠቀምበት ነው። ሀገር የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝና እድገቷን እንድታፋጥን በማለም ነው። እናም የዛሬ ሀገር ተረካቢዎች በዚህ ልክ አስበን እንጠቀምበት ማለት እንወዳለን።

በጊቤ ሦስት የኃይል ማመንጫ አማካኝነት ከተፈጠረው ሰው ሠራሽ ሐይቅ ዳርቻ የሚገኝ በመሆኑ ጠቀሜታው ቀላል አይደለም። በተለይ አሁን ከተያዘው ‘ገበታ ለሀገር’ ኮይሻ ኮሪደር ፕሮጀክት ውስጥ ተካቶ የሚለማ እንዲሁም ባሕላዊ ሙዚየሞችና የምርምር ማዕከላት እንደሚቋቋምለት የሚደረግ ስለሆነ ለራሳችን ደስታና የገቢ ምንጭ፣ ለሌሎች እረፍትና የሥራ እድል ማግኛ እናድርገው በማለት ለዛሬ ሀሳባችንን አበቃን። ሰላም!!

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ለሰላም ተምሳሌት የሆኑት ማኅበራት

አስናቀ ፀጋዬ



የኦሮሚያ ወጣቶች ማኅበር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወጣት ገዛኸኝ አንዳርጌ



የአማራ ወጣቶች ማኅበር ዋና ፀሐፊ ወጣት ከፍያለው ማለፉ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው። ለዘመናት አብሮ ተከባብሮ በመኖርና የሰላም ተምሳሌት በመሆን በአርአያነት ሲጠቀስ የኖረ ሕዝብ ነው። ከኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ አኩሪ መገለጫዎች መካከል የብሔር፣ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባሕልና ሌሎች ልዩነቶችን ዕውቅና በመስጠት ተሳስቦና ተከባብሮ መኖር ትልቁ እሴት ነው። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ሰላም መገለጫቸውና የመጀመሪያ ምርጫቸው ነው። ለሰላም ሲሉ በርካታ መስዋዕትነቶችን ይከፍላሉ።

ሆኖም ይህንን ሰላም ወዳድ ሕዝብ የሚበጠብጡ፤በሀገሩ በሰላም ወጥቶ እንዳይገባ ድንጋይ የሚፈነቅሉ፤ጦር የሚሰብቁና መሣሪያ የሚመዙ የሞት ነጋዴዎች በርካቶች ናቸው። በነዚህ የእኩይ ሰዎች ጦስም ሰዎች ለሞት፤ለሥደት፤ለመፈናቅ፤ለመከራና ሥቃይ ይዳረጋሉ፡፡

የዚህ ሁሉ ሰለባና ገፈት ገማሽ ከሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ዋነኛው ደግሞ ወጣቱ ነው። በመሆኑም ወጣቱ የሰላም ዋጋን ተረድቶ ፊቱን ወደልማት በማዞር ራሱን መጥቀምና ለሌላውም መትረፍ እንዳለበት የአብዛኞች ምኞትና ፍላጎት ነው። ወጣቱ ለሰላም ዘብ ሆኖ በልማት ተጠቃሚ እንዲሆን ታዲያ የየድርሻቸውን እየተወጡ መሆኑን የአማራና የኦሮሚያ ወጣት ማኅበራት ይገልፃሉ።

ወጣት ከፍያለው ማለፉ የአማራ ወጣቶች ማኅበር ዋና ፀሐፊ ነው። እርሱ እንደሚለው ማኅበሩ ከሕግ ማስከበር ዘመቻው ጀምሮ በርካታ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል። ከነዚህ ውስጥ ደግሞ ዋናው በሁሉም የክልሉ ከተሞች ላይ ሰርጎ ገቦችን ከመከላከልና ከፀጥታ መዋቅር ጋር በመሆን በየአካባቢው ሰላምና ፀጥታ እንዲረጋገጥ ጥበቃ የማድረግ ሥራ ነው። ለዚህም በጊዜው የግንዛቤ መስጫ መድረኮች ሲያካሂድ ቆይቷል። በተለይ ደግሞ ከባሕርዳር ዩኒቨርስቲ መምህራን ጋር በመሆንና ትላልቅ የግንዛቤ መድረኮችን በመፍጠር ለወጣቶች ሥልጠና በመስጠት ግንዛቤያቸው እንዲሰፋና የክልላቸውን ሰላም እንዲጠብቁና በልማት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ አድርጓል።

እንደወጣት ከፍያለው ገለፃ፤ የንቅናቄና ግንዛቤ መድረኮቹ 20 ሰዎችን በመመደብ አሥሩ በጎንደር ማዕከል እስከ ሑመራ ድረስ፤ አሥሩ ደግሞ በጎጃም ሰሜን ሸዋ ደሴ ድረስ ሲካሄዱ ቆይተዋል። በዚህም እንደማኅበር የክልሉን ሰላም ከመጠበቅ አንፃር ጥሩ ሥራ ተሠርቷል።

በአሁኑ ግዜም የወልቃይት፣ ራያ፣ አጣዬ እና የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር መሥመር የክልሉ የሰላም ሥጋት ናቸው ብሎ በመለየት የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። በተለይ ደግሞ የአጣዬ መሥመር የውስጥ ኃይሎችም ጭምር የተሳተፉበት ጥቃት በተደጋጋሚ ይከሰታል። ሕዝቡ ወደሰላም እንይመለስና ተረጋግቶ እንዳይኖር፤ ብሎም እርስ በርሱ እንዲጋጭ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ። ይህም ለመላው የክልሉ ነዋሪና ወጣቱ ኅብረተሰብ ትልቅ ሥጋት ነው።

በአጣዬ አካባቢ ያለው ሁኔታ ግን መንግሥት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ችግሩ በተደጋጋሚ የሚከሰትና ማብቂያ ያላገኘ በመሆኑና ድርጊቱም በተቀነባበረና በተጠና ሁኔታ የሚፈፀም በመሆኑ ወጣቶች ለጉዳዩ ምላሽ ሊሰጡበት የሚችሉት ጉዳይ አይደለም። ከፀጥታ መዋቅሩ ጎን ከመቆም፣ አጋዥ ከመሆንና ድርጊቱን ከማውገዝ በዘለለ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር የለም። ለዛም ነው የመንግሥት ትኩረት የሚያስፈልገው። በአግባቡ ተጠንቶና ፖለቲካዊ ትርጉም ተሰጥቶት ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ ስለሆነ የፖለቲካ አመራሩም በደምብ አጥንቶ ምላሽ መስጠት አለበት።

ነገር ግን ወጣት ማኅበሩ እንደክልልም እንደሀገርም ለሰላም ከክልሉ ውጪና ባሻገር ከሌሎች አጎራባች ክልሎች ጋር በጋራ እየሠራ ይገኛል። ለአብነትም ከኦሮሚያ ወጣቶች ማኅበር ጋር በቅርቡ በአዲስ አበባ መድረክ ነበረው። ዋነኛ የውይይቱ አጀንዳም የሚያጠነጥነው፤ እንደ አንድ ሲቪክ ድርጅትና ገለልተኛ ተቋም መንግሥት የሚያጠፋቸውን ጥፋቶች በማሳየት፤ የሚያለማቸውን ደግሞ በመደገፍ ገለልተኛነትን በመጠበቅና አንድ ሆኖ በመቀጠል እንዴት የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንደሚቻል ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ወጣቶች ምን ዓይነት ፋይዳ ይኖራቸዋል? የሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ መሆን ለወጣቶች ምን ትሩፋቶችን ይዞ ይመጣል? ውድቀቱ ምን ጉዳት ይዞ ሊመጣ ይችላል? በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያም ውይይት ተደርጓል። የክልሎች ከክልሎች በተለይ ደግሞ በወጣቶች ደረጃ ግንኙነቶችን ለማጠናከርም ከመግባባት ላይ ተደርሷል።

በቀጣይም የአማራና የኦሮሚያ ወጣቶችን የሚያቀራርቡ ተመሳሳይ የአንድነትና የአብሮነት ውይይት መድረኮች በጅማና ጎንደር ከተሞች ይደረጋሉ። ሁለቱ መድረኮች በስኬት የሚጠናቀቁ ከሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁሉም የየክልሎች ወጣቶች የሚገናኙበት አንድ መድረክ ለማካሄድ በማኅበሩ በኩል ታስቧል። በተጨማሪም የአማራ ምሑራንና ተፅዕኖ ፈጣሪዎች በተገኙበት አንድ የውይይት መድረክም በቅርቡ በክልል ደረጃ ያካሂዳል።

የመድረኩ ዋነኛ ማጠንጠኛም አሁን የመጣውን ሰላም አስተማማኝ አድርጎ ከማስቀጠል አኳያና ወጣቱ ወደልማት እንዲገባ በማድረግ በኩል የተፅዕኖ ፈጣሪ ወጣቶችና አክቲቪስቶች ሚና ምን ሊሆን ይችላል ነው። በጥቅሉም ክልሉ ሰላም እንዲሆንና ባለፈው ወር የጥምቀት በዓልና ሌሎችም በዓላት በሰላምና በስኬት ተከብረው እንዲጠናቀቁ በሁሉም አካባቢዎች ያሉ የክልሉ ወጣቶች ትልቅ አስተዋፅዖ አድርገዋል። በሕግ ማስከበር ዘመቻው ወቅትም በተለይ በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ሆስፒታሎች ውስጥ በበጎ ፍቃድ ቁስለኞችን የመንከባከብ ሥራዎችን አከናውነዋል።

ወጣት ከፍያለው እንደሚለው፤ በአማራ ክልል በርካታ ሥራ አጥ ወጣቶች አሉ። እስካሁንም መንግሥትም ሆነ ሌሎች የግል ተቋማት በቂ ምላሽ እየሰጡ አይደሉም። ወጣት ማኅበሩ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ ለመሥራት ያሰበውም የክልሉ ፈተና ሆኖ በቀጠለው የሥራ አጥነት ጉዳይ ላይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ባለሃብቶችና ሥራ እድል ሊፈጥሩ የሚገባቸው ተቋማት በተለይ ደግሞ መሬት ወስደውና አጥረው የተቀመጡ፣ ትላልቅ ድርጅትም ኖሯቸው የሥራ እድል ያልፈጠሩ በአንፃሩ ደግሞ የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች ዝቅተኛ ተከፋይ ስለሆኑ ኑሯቸውን መግፋት ባለመቻላቸው በዚህ ላይ ማኅበሩ ትኩረት አድርጎ ይሠራል።

በተለይ ግን የሥራ ፈጠራው ጉዳይ በክልሉ የወጣቱ መሠረታዊ ችግር በመሆኑ ለክልሉ ሰላም እጦት የራሱን አስተዋፅዖ የሚያበረክት በመሆኑ የማኅበሩ ዋነኛና ቀጣይ የሥራ እድል ፈጠራ ላይ ነው። ከዚሁ ጎን ለጎን ግን በክልሉ ሰላም እንዲረጋገጥና ወጣቱ በአመክንዮ የሚታገልና በሀሳብ ትግል ነገሮችን ለመፍታት የሚሞክር እንዲሆን ተከታታይነት ያላቸው መድረኮች በየክልሉ ከተሞች ይካሄዳሉ።

ይህ ወጣት የዚች ሀገር ባለቤት እንደመሆኑ ከአባቶቹ የተረከባትን ሀገር የማስቀጠልና ለቀጣዩ ትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት አለበት። ይህን ማድረግ የሚችለው ደግሞ በተረጋጋ መንፈስ፣ በሀገራዊ አንድነትና ከብሔርተኝነት አስተሳሰብ በፀዳ መልኩ ነው። ወጣቱ ምክንያታዊና ሚዛናዊ ሀሳብ በማንሸራሸር፣ በመተጋገዝና በመደጋገፍም ጭምር እስካልቀጠለ ድረስ አብሮ የመቀጠሉና ችግር ውስጥ የመውደቁ እድል ሰፊ ነው። ስለዚህ ወጣቶች የአብሮነትን ጉዳይ አትኩሮ ሊጠብቀው ይገባል። ለአንድነቱ ጉዳይ መደራደር የለበትም። ለሰላምም ዘብ መቆም ይኖርበታል።

የኦሮሚያ ወጣቶች ማኅበር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወጣት ገዛኸኝ አንዳርጌ በበኩሉ፤ እንደሚለው በክልሉ ያለው የሰላም ሁኔታ ከቦታ ቦታ ይለያያል። ከሸኔ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች በተለይ ደግሞ በምዕራብ ኦሮሚያ ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የፀጥታ ችግሮች አሉ። ይህ ችግር ይበልጥ የተባባሰውም ከሰሜኑ ጦርነት ጋር በተያያዘና የመንግሥት ሙሉ ኃይል ወደዚያ በመሄዱ ነው።

ይሁንና በአሁኑ ጊዜ የሰሜኑ ጦርነት ስለተቋጨና ሰላም ስለመጣ በሰሜኑ በኩል ያለው ኃይል ወደምዕራብ ኦሮሚያ መጥቶ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። በዚህም ትልቅ ለውጥ እየመጣ ነው። አንዳንድ የሸኔ አባላትም በሰላማዊ መንገድ ገሚሶቹ ለአባገዳዎች ሌሎች ደግሞ ለፀጥታ ኃይሎች እየሰጡ ነው። ይህ ሲባል ግን የተሟላ ሥራ ተሠርቷል ማለት አይደለም። አሁንም ተጨማሪ የፖለቲካና የአደረጃጀት ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

የክልሉ ወጣት በአብዛኛው ሥራ አጥ በመሆኑ ሰላምን ከማንም በላይ ይፈልገዋል። ለሰላም ሲልም ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሏል። ይሁንና ሰላም እንዳይኖርና ወጣቱም ሥራ እንዳይሠራ፣ ትምህርቱንም እንዳይከታተል የሚያደርጉ ሌላ ተልዕኮ ያላቸው አካላት አሉ። ዓላማው ሳይገባቸው በተሳሳተ መንገድ ከነዚሁ አካላት ጋር ሆነው የሚሠሩ ወጣቶችም አሉ። ሰላምና መረጋጋት ቢኖር ግን ቁጭ ብሎ በመወያየትና ወጣቱም ሥራ ፈጥሮ መሥራትና ራሱን መለወጥ ይችላል። ከዚህ አንፃርም የክልሉ ወጣት በማኅበረሰቡ ውስጥና በበጎ ፍቃድ ሥራዎች ላይ በቀዳሚነት እየተሳተፈ ይገኛል። ሥራ ሳይኖረው ለመለወጥና ለእድገት ያለው ፍላጎትም ከፍተኛ ነው።

እንደ ወጣት ገዛኸኝ ገለፃ፤ የሰላም ችግር የሚመጣው ካለመረጋጋትና በፖለቲካ ሽኩቻ በሚመጡ ችግሮች ነው። የክልሉ ወጣት ማኅበር ሥጋትም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው የፖለቲካ ፍላጎት ከብሔር ጋር መገናኘት ነው። ለአብነትም የተረኝነት ነገሮችና ሌሎችም ከብሔር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ይነሳሉ። እንደዚህ አይነት ነገሮች ደግሞ ወጣቱን ስሜታዊ በማድረግ ወደተሳሳተ አቅጣጫ ይመሩታል። ስለሆነም መከባበርና መተሳሰብ ያስፈልጋል።

ከዚህ አንፃር ሰው ተረጋግቶ እኔ ብቻ ከሚለው አስተሳሰብ ወጥቶ እኛ ወደሚለው ከመጣ ሰላምና አንድነትን ማረጋገጥ ይቻላል። ማኅበሩም ወጣቱ በሰከነ መንገድ ነገሮችን በማየትና በማመዛዘን ወደፊት እንዲሄድ እየሠራ ይገኛል። በዚህም በርካታ ለውጦች እየመጡ ነው። ነገር ግን ይህ ብቻውን በቂ ባለመሆኑ በተለይ ይህን በማጉላት ረገድ ሚዲያዎች ትኩረት አድርገው ሊሠሩ ይገባል። መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በወጣቱ ስብዕና ግንባታ ላይ ብዙ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ይህን ማድረግ ከተቻለም የተሻለች ኢትዮጵያን ማየት ይቻላል።

በክልሉም ሆነ በሀገሪቱ የተሻለ ሰላም እንዲመጣ በወጣቱ ላይ መሥራት ያስፈልጋል። በተለይ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች በመኖራቸው ብሔርን ከብሔር ጋር ለማጋጨት የሚሠሩ አካላት ከድርጊታቸው ሊታቀቡ ይገባል። ከዚህም ባሻገር ታች ወርዶ የሕዝቡን በዋናነት ደግሞ ወጣቱ ፍላጎት ምን እንደሆነ ለማወቅ ማወያየት ያስፈልጋል።

ወጣት ማኅበሩም በክልሉ ምንም ዓይነት የሰላም ችግር እንዳይፈጠር ይሠራል። ሰላምን ለማስጠበቅ ደግሞ እንደወጣት አደረጃጀትና እንደክልሉ ብሔር ብሔረሰቦች ወጣቶች ሰፊ ርብርብ እያደረገ ይገኛል። ይህም በቀጣይ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። ወጣቱ ለሰላም በነፃ እየሠራ ያለውም ለሕዝቡና ለሀገሩ ሲል ነው።

ይሁንና ራሳቸው ሳይነኩ ወጣቱ በተለያዩ ነገሮች ሰለባ እንዲሆን የሚሠሩና ብሔርን ከብሔር ጋር ለማጋጨት የሚጥሩ ሰዎች ከዚህ ሥራቸው መቆጠብ አለባቸው። ከዚህ ይልቅ ቁጭ ብሎ መወያየትና መነጋገር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ማኅበሩም ከዚህ ወዲያ በእንዲህ አይነቱ ድርጊት ውስጥ በሚሳተፉ አካላት ላይ የራሱን አቋም ይወስዳል። ምንም ዓይነት የፀጥታ ችግር እንዲፈጠርም አይፈልግም።

ወጣቱ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው። ነገር ግን ደግሞ ወጣቱ እስከዛሬ ድረስ በተለያዩ ነገሮች ሰለባ ሆኗል። ይህ ነገር ደግሞ አሁንም መቀጠል የለበትም። ሥራውን ተረጋግቶ መሥራት አለበት። ራሱንና ሀገሩንም መለወጥ ይጠበቅበታል። ለዚህ ታዲያ የሰላም ዋጋ ምን ያህል ውድ መሆኑን ተረድቶ ፊቱን ወደሰላም ማዞር ይኖርበታል።

# የምድር በረከት

# የማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚውን የልማት አጀንዳ በማድረግ የተፈጠረ መነቃቃት - በአማራ ክልል

**ስምስም መንግሥቱ**

በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረጉ አንዳንድ የዳሰሳ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ በማዕድን ልማት ዙሪያ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ ነው። በዚህ ዘርፍ ላይ ጥቂት ሰዎች እውቀቱና መረዳቱ ቢኖራቸውም፣ አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል ግን ውስን መረጃ እንዳለው ይታመናል። ይህም መንግስትም ሆነ ባለድርሻ አካላት ማህበረሰቡ ስለ ማዕድን ሀብት ልማትና ትግበራ እውቀት፣ ግንዛቤና መረዳት እንዲኖረው ከማድረግ መጀመር እንዳለበት ያስገነዝባል።

ስለ ማዕድን ልማትና አስፈላጊነቱ የተረዳ ማህበረሰብ መፍጠር ከተቻለ የአገሪቱ ሀብት ለግለሰቦች መጠቀሚያ እንዳይውል በመከላከልና በመጠበቅ፣ ዘርፉ ለሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት ሊኖረው የሚችለውን ፋይዳ እንደሚያጎላው እንደሚያደርግ ባለሙያዎች ምክረ ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡

የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ የበጀት አመት እቅድ ሥራም ይህንኑ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን የቢሮውን የ2015 በጀት አመት የስድስት ወር የእቅድ አፈጻጸም ስንቃኝ ለመረዳት ችለናል። ቢሮው በበጀት አመቱ ስድስት ወር ምን አቅዶ ምን ፈጸመ በሚል የጠየቅናቸው የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ታምራት ደምሴ እንዳሉት፤ ቢሮው ወደ እቅድ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የእቅዱ አካል የሆነውን የንቅናቄ መድረክ አካሂዷል። ቢሮው ዘርፉን ለመምራት የሚያስችለውን አደረጃጀት መፍጠር የቻለው በቅርብ ጊዜ በተለይም የማዕድን ዘርፉ እንደ ሀገር በልዩ ትኩረት እንቅስቃሴ ከጀመረ ወዲህ ነው፡፡

የቢሮ አደረጃጀትና መዋቅሩ ሲጠናከር በዘርፉ የሚያከናወኑ ተግባራትም ውጤት የሚያስገኙ መሆን ስላለባቸው የንቅናቄ ሥራን በማስቀደም ነው ወደ ዋና ትግበራው የገባው። ሀብቱና ከሀብቱ የሚገኘው ገቢ በሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ላይ ስላለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ብቻ ሳይሆን፣ ልማቱ የሚከናወንበት አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ተጠቃሚነት እንዲጠበቅም ነው። ልማቱ በቴክኖሎጂ ሲታገዝና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ቀድሞ ግንዛቤ ከተያዘ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመቀነስ ያስችላል ከሚል እሳቤ በመነሳት እንደሆነም አቶ ታምራት ገልጸዋል፡፡

‹‹አልሚው ካልመጣ ልማቱ አይኖርም። እንዲመጣ ደግሞ መርጦ ለማልማት እንዲያስችለው ያለውን ሀብት ቀድሞ ማስተዋወቅና ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል›› የሚሉት አቶ ታምራት፤ የንቅናቄ መድረኩ ቀድሞ መከናወኑ የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ አልሚውን በመረጠው ዘርፍ ለመሰማራት እንዲሁም የማዕድን ሀብቱና የሚገኝበትን አካባቢ ማሳወቁ አስፈላጊነቱ ጉልህ ሆኖ መገኘቱን ይገልፃሉ። ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ባለው አመራር እንዲሁም በተለያየ መንገድ የሚመለከተው ባለድርሻ አካልና በማህበረሰብ ዘንድ የማዕድን ዘርፉ ከድህነት መውጫና የብልጽግና መንገድ መሆኑን አጀንዳ እንዲሆን የንቅናቄ መድረኩ ትልቅ ትርጉም እንደነበረው አስታውሰዋል።

በአማራ ክልል ከቢሮ አደረጃጀት ጀምሮ ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት እንዲሁም የልማቱም ተጠቃሚነት አነስተኛ እንደነበር የተናገሩት አቶ ታምራት፤ መንግሥት በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር አመት መሪ እቅድ ማዕድንን የሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት አንዱ አድርጎ ስለመረጠው ንቅናቄውም አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የንቅናቄው ዓላማ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ግንዛቤ ፈጥሮ ወደ ሥራ መግባት ነው። ‹‹ማዕድን አዲስ የንጋት ተስፋ ለክልላችን፣ ለሀገራችን›› በሚል መሪ ቃል በተካሄደው የንቅናቄ መድረክ በዞንና በወረዳ ጭምር የተሳካ ተግባር ተከናውኗል። ንቅናቄው አልሚዎችን ጨምሮ ወደ 9ሺህ 807 የሚሆኑ ባለድርሻ አካላትን ተደራሽ ያደረገም ነው።

በዚህ የዝግጅት ምዕራፍ ቢሮው ሌላው ያከናወነው ተግባር ለአሰራር ማነቆ የሆኑ መመሪያዎችን በማሻሻል የዘርፉን የልማት ሥራ የሚመጥኑ ህጎች መተግበር ነው። በክልሉ የሚገኙ የማዕድን አይነቶችና የሚገኙባቸውን አካባቢዎች የሚያመላክት ፍኖተ ካርታ (ማፕ) ከማዘጋጀት ጀምሮ ክልሉ በማዕድን ሀብት የሚገኝበትንም ደረጃ በመረጃ ለማስደገፍ ቢሮው በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የተቀናጀ ሥራ በመሥራት ያደረገው ጥረትም ውጤታማ መሆኑ የስድስት ወር ግምገማው ያሳያል። በጥናት የተደገፈ ሥራ መረጃ ሲኖር ሀብትን ለይቶ ለኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግም ሆነ ከሀብቱ የሚገኘውን ጥቅም ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል እንደሆነም ቢሮው ከተከናወነው ተግባር መገንዘብ ችሏል፡፡

ክልሉ የማዕድን ልማት ቀጠናውን አንድ በመቶ ሺህ ካሬ ሜትር በሆነ መስፈርት መለየትና መከለል ቢሮው ካከናወናቸው አበይት ተግባራት መካከል ይጠቀሳል ያሉት አቶ ታምራት፣ ለግብርና እና ለሌሎች ልማት ከሚውለው መሬት የማዕድን ልማት ቀጠናዎችን ለይቶ መያዝ አልሚውን በቀላሉ በልማቱ ለማስማራት ጠቀሜታው የጎላ ሆኖ ተገኝቷል ሲሉ ያብራራሉ። በዚሁ መሠረትም ቢሮው ወደ 20ሺ ካሬ ሜትር መሬት በመለየት ለኢንቨስትመንት ምቹ አድርጓል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ በክልሉ አዊ ዞን፣ ዳንግላ ወረዳ፣ ሰሜን ሸዋ አንኮበር፣ ደቡብ ወሎ አምባሰል፣ ዋግ ኽምራ ሰቆጣ ወረዳ፣ ሰሜን ጎንደር ጃንአሞራ አካባቢዎች የርቀት የዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ በማድረግ የመጀመሪያውን ምእራፍ ስራ አጠናቅቋል። በዳሰሳ ጥናቱ መሠረትም ከ40 በላይ የማዕድን አይነቶችን መለየት ተችሏል። ቢሮው በጥናት የተደገፈ ሀብትን ከመለየትና ለኢንቨስትመንት ምቹ ከማድረግ አኳያ ያከናወናቸው ተግባራት በአዲስ ተደራጅቶ ወደ ሥራ የገባ በመሆኑ አፈጻጸሙ ለቀጣይ ስድስት ወራት ሥራው ተስፋ ሰጪ ሆኖ ተገኝቷል።

በቅድመ እቅድና ትግበራ ሥራ በተለይም በጥናት በመለየት ለኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግ በተከናወነው ተግባር ከተመዘገበው ውጤት በቢሮው የማምረት ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ ከገቡት አልሚዎች አንድ የሲሚንቶና አንድ የጂብሰም ቦርድ ፋብሪካዎች ይጠቀሳሉ። 12 ኩባንያዎችም የወርቅ ማዕድን ምርመራ ፍቃድ ከቢሮው የወሰዱ ሲሆን፣ በድንጋይ ከሰል እና በብረት ማዕድን ልማት ላይ በተመሳሳይ ቢሮው ፍቃድ ሰጥቷል፡፡

በመንግሥት ከተቀመጡት የትኩረት አቅጣጫዎች በማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚው ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር በመሆኑ ቢሮው በበጀት አመቱ ለ52 ሺህ 858 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ከያዘው እቅድ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለ18 ሺህ 228 ዜጎች በዘርፉ የሥራ እድል ፈጥሯል።

በቅድመ እቅድ የተከናወኑት ተግባራት የመጨረሻ ግባቸው ገቢ ማስገኘት በመሆኑ፣ በዚህ ረገድ በተለይም የውጭ ምንዛሬን በማስገኘት የተከናወነውንም ሲገልፁ፤ ክልሉ ከጌጣጌጥ ማዕድናት በኦፓል ማዕድን እንደሚታወቅ አንስተዋል። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በእቅድ የተያዘው 28ሺህ 531 ኪሎ ግራም ሲሆን፤ በስድስት ወር ክንውን 14ሺህ 268 ኪሎ ግራም ኦፓል ለውጭ ገበያ ቀርቧል። በገቢም ከኦፓል ልማት በበጀት አመቱ አጠቃላይ እቅድ የተያዘው 15 ነጥብ ሁለት ሚሊየን ዶላር ገቢ ለማግኘት እንደሆነና በስድስት ወር አንድ ሚሊየን 692 ሺህ 872 ነጥብ 42 ዶላር ገቢ ከዘርፉ መገኘቱን አቶ ታምራት ገልጸዋል፡፡

ክልሉ በበጀት አመቱ 70 ኪሎ ግራም ወርቅ ለማልማት ታቅዶ እንደነበርም አቶ ታምራት ጠቁመዋል። በዚህም ወደ 84 ነጥብ 98 ኪሎ ግራም በማልማት ከእቅድ በላይ መፈጸም መቻሉን ገልፀው፣ የለማው ወርቅም ለብሄራዊ ባንክ መቅረቡንም አስታውቀዋል። ከዘረፉ አራት ሚሊየን 928ሺህ 840 ዶላር ገቢ እንደተገኘም ይናገራሉ። ከማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚው ጋር በተያያዘ በሀገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ ተብለው



**አቶ ታምራት ደምሴ፤**

በእቅድ ከተያዙት ከተለያዩ የአገልግሎት ክፍያዎችም ገቢ መገኘቱን ጠቅሰው፣ 100 ሚሊየን 400 ሺህ ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ፣ 16 ሚሊየን 112ሺህ 656ብር መገኘቱን አመልክተዋል፡፡

የውጭ ምንዛሪ ወጪን በማዳን ደረጃም ክልሉ የተለያዩ ተግባራት ማከናወኑን የጠቆሙት አቶ ታምራት፣ በበጀት አመቱ ግምሽ አመት አፈጻፀም ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ግብአት የሚውሉ እንደ ጂብሰም፣ ላይምስቶን፣ ሸክላ አፈር የመሳሰሉ ማዕድናት በማልማት ወደ 27 ሚሊየን ዶላር የሚገመት የውጭ ምንዛሪ ማዳን መቻሉን አስረድተዋል። በበጀት አመቱ በሀገር ውስጥ በማምረት ለመተካት በእቅድ የተያዘው አንድ ሚሊየን 37ሺህ 02 ቶን ማዕድን መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ቢሮው በአዲስ መልኩ ከመዋቀሩ ጋር ተያይዞ በበጀት አመቱ ስድስት ወራት አብዛኛው የሥራ እንቅስቃሴ በቅድመ ዝግጅት ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን አቶ ታምራት ገልጸውልናል። ያም ሆኖ ግን የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት፣ በሀገር ውስጥም ከተለያዩ አገልግሎቶች የተገኘው ገቢ ለቀጣይ ሥራ ተስፋ ሰጭ መሆኑና ውጤት መመዝገቡን አመራሩ በግምገማው ማስቀመጡን ያስረዳሉ። በመዋቅር ደረጃ ዘርፉን ብቻ የሚመራ ዘርፍ የተፈጠረበት፣ በክልሉ 13 ዞኖች በመመሪያ ደረጃ መዋቀሩና በ45 ወረዳዎች ውስጥም በተመሳሳይ አደረጃጀቱ መጠናከሩ እንደ አንድ ስኬት መወሰዱን ይገልፃሉ።

ከህገወጥ ንግድ ጋር በተያያዘም የነበረውን ሁኔታ በወርቅ ማዕድን ላይ ክትትልና ቁጥጥሩ የላላ፣ ለሌሎች መጠቀሚያ ሲውል እንደነበር አስታውሰው፤ በተያዘው በጀት አመት በክልሉ በወርቅ ማዕድን የተመዘገበው ውጤት ከዚህ ቀደም ያልተገኘ እና ለብሄራዊ ባንክም የቀረበበት ጊዜ መሆኑን አመልክተዋል።

ውጤቱ በስኬት ቢወሰድም በበጀት አመቱ ካጋጠሙት ተግዳሮቶች መሻገር ያልተቻለው ህገወጥ የማዕድን ንግድን መቆጣጠር አለመቻልን እንደሆነ አቶ ታምራት ይናገራሉ። በአልሚዎች በኩል ለማልማት ፈቃድ ወስደው ቶሎ ወደ ሥራ አለመግባትና መሬት አጥሮ ማስቀመጥ ጉዳይም ሌላው ተግዳሮት እንደሆነም ይጠቅሳሉ። ያለው ሁኔታም በቀጣይ ፍቃድ የመሰረዝ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስገድድ እንደሆነም ነው ያመለከቱት፡፡

የተሟላ መሠረተ ልማት አለመኖርም በማዕድን ልማቱ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እንቅፋት እንደሆነ ቢሮው የለየው ችግር መሆኑን ጠቅሰዋል። በተለይም ልማቱ የሚከናወንበት ሥፍራ የሚያስገባ መንገድ ችግር መቀረፍ እንዳለበት ታምኖበታል። ወደ ማዕድን ልማቱ የሚመላለሱ ተሽከርካሪዎች ጠንካራ መሆን እንዳለባቸው ያለው ነባራዊ ሁኔታ ያስገድዳል ያሉት አቶ ታምራት፣ መንግሥት እነዚህ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚፈቀድበትን ሁኔታ ቢያመቻች ባለሀብቱን የበለጠ ያነቃቃዋል ይላሉ።

እንደ ድንጋይ ከሰል ማምረቻ ላሉ ፋብሪካዎች የሚውል የኃይል አቅርቦትም ወሳኝ እንደሆነ ጠቁመዋል። በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረው ጦርነት ዘርፉ ትልቅ ችግር ውስጥ ወድቆ እንደነበር አስታውሰዋል። የጦርነቱ መቆም አንድ ትልቅ ነገር መሆኑን ጠቅሰው፣ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ እንደልብ ለመሥራት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ ተስፋ ሰጪ ሆኖ መገኘቱን ገልጸዋል። በክልሉ በዘረፉ መሰማራት ለሚፈልጉ ሁሉ በክልሉ ምቹ ሁኔታ መኖሩን ጠቅሰው፣ አቶ ታምራት ጥሪ አቅርበዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## አደራ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

እለተ ቅዳሜ በወበቃማው አየር ድብትብት ብላለች። መጣ ሄድ የሚል አይናፋር ንፋስ በእሳታማዋ ጀምበር እየተገላመጠ ይመለሳል። የአርባ ስድስት አመቱ ቢሆነኝ በዳዴ የሚሄድ ልጁን ጭኑ ላይ አስቀምጦ ያጫውተዋል። በፈገግታው ውስጥ አለምን እያየ፣ በፀዓዳ ሳቁ ሐሴት እያደረገ። ምን እንደሚለው አይገባውም.. ብቻ ግን ያወራዋል..ፍጹም የሆነ እውነት..ድንቅ የሆነ ነገር። የተጨበጠ እጁን ወደ አፉ እያለ፣የሚዝረከረክ ለሀጩን ወደ ጭኑ እያንጠባጠበ እንደዚህ፡፡

በረቀቀ አባታዊ ፍቅር አየው..በረቀቀ አባታዊ ስስት ወደ ደረቱ አስጠግቶ አቀፈው። በልጁ ውስጥ ብዙ እውነት ታየው.. ለዘመናት ፈልጎ ያጣውን የአባቱን እውነት በልጁ ነፍስ ውስጥ አገኘው፡፡

ደጋግሞ ሳመው..። እንደ መገበሪያ ስንዴ የሚያሳሳ ጉንጩ..ለዘላለም በንጽሕና የሚታወሱ አይኖቹ የጠፋበትን እውነት ነገሩት። አባቱ እውነቴ አንተ ነህ.. ከእንግዲህ በአንተ እኖራለሁ አንተም የሚያኖርህን እውነት ፈልግ..የእውነትህን ስፍራ ድረስበት ብለውት ነበር። እውነቱን በልጁ ነፍስ ውስጥ አገኘው። አባቱ ምን ያክል ጠቢብ እንደሆኑ በደንብ የገባው ዛሬ ነው.. አባት ከሆነ በኋላ። ኢትዮጵያዊነትን ያስተማሩት፣ሀገርና ታሪክን ያወረሱት አባቱ ናቸው። ፍቅርን ትህትናን ያለበሱት እሳቸው ናቸው። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በልጅነት ልቡ ውስጥ ያስቀመጡት አባቱ ናቸው። የአባቱ ትሑታን ንግግሮች በሕይወቱ ሁሉ ይከተሉታል። ዛሬም በጎልማሳነት እድሜው እየተከተሉት ነው። የአባቱን እውነት ለልጆቹ ሊሰጥ ለራሱ ቃል ገባ፡፡

ጆሮውን ወደ ሳሎን ወረወረ..የእናትና ልጅ ፍቅር ተሰማው። መጠየቅ የማይሰለቸው ልጃቸው እናቱን በጥያቄ እያስጨነቀ ሲያጉተመትም.. በልጁ ጥያቄ ልቧ የወለቀ ግን ደግሞ ደስተኛ እናት ለባልና ለልጆቿ ራት ልትሠራ ምድጃው ስር አጎንብሳ ታየችው። እየተቆጣች የምትራራ፣እየተከፋች ይቅር የምትል፣ እያዘነች የምትጽናና ነፍስ ፊቱ ድቅን አለች። አባቱ ሀገር የቤተሰብ ነጸብራቅ ነው ይሉት ነበር። አንተን እንዲህ የማሳድግህ ነገ ላይ ከኔ የወረስከውን እውነት ለልጆችህ እንድትነግራቸው ነው እንዲህም ይሉት ነበር። አባቱ ብዙ እውነቱ..ብዙ እውቀቱ ናቸው። በሕይወቱ ሁሉም ቦታ ላይ አሉ። ጎልምሶ እንኳን በአባቱ እውነት ነው የሚኖረው። ከነገሩት እውነት ሁሉ ግን ‹ሀገር ነፍስ የላትም..ሀገር እኔና አንተ ነን። ሀገር የኔና የአንተ የሌላው ሰው ሰውነት ነው። ሀገር የእኔና የአንተ የሌላው ሰው የጋራ ቀለም፣ የጋራ አስተሳሰብ፣የጋራ ባሕልና እሴት ነው። ሀገር ሌላውን በመውደድ የሚገለጽ ነው። የሀገር ፍቅር በሌሎች ልብ ውስጥ ሕያው ሆኖ መብቀል ነው ያሉትን አይረሳውም። በዚህ እውነት ውስጥ እንዲኖርም አደራ ብለውታል። ዛሬ ለእሱ ሀገር የአባቱ አስተሳሰብ ናት። ዛሬ ለእሱ ኢትዮጵያዊነት የአባቱ የአደራ ቃል ናት። ዛሬ ለእሱ ሀገር መውደድ በሌሎች ልብ ውስጥ ሕያው ሆኖ መብቀል ነው። ከአባቱ ለምዶበት የሚወደውን ነገር በሀገሩ መመሰል ይወዳል። አባቱ በልጅነቱ ጭናቸው ላይ አስቀምጠውት ሀገሬ ነህ ይሉት ነበር። እሱም ዛሬ ልጁን ጭኑ ላይ አስቀምጦ ሀገሬ ነህ አለው። ያለው የገባው ይመስል ትንሹ ልጅ ሳቀ..የአባቱን ደረት በእጆቹ እየጠበጠበ ከተንስኦ የጣመ ድምጹን አሰማ። ሳቁ ሰማየ ሰማያት ደርሶ ተመለሰ፡፡

ከእናቱ ጋር ሳሎን ሲነታረክ የነበረው ልጅ ያኮረፈ ፊቱን ይዞ ወደ አባቱ መጣ። ገና ከመድረሱ..እናቱ የቤት ሥራውን ማታ ነው የምሠራልህ ስላለችው እንዳኮረፈ ነገረው፡፡

‹ይሄ እኮ የሚያስኮርፍ ነገር አይደለም...አሁን ሥራ ላይ ስለሆንኩ ማታ እሠራልሀለሁ ማለት እኮ እምቢ ማለት አይደለም። ሁሉም ነገር ጊዜ አለው..ያንን ጊዜ የመጠበቅ ትዕግስት ሊኖርህ ይገባል፡፡

‹ትዕግስት ምንድነው? ልጁ ጠየቀ፡፡

መጠበቅ..በጽናት በእምነት መጓዝ፡፡

‹ግን እኮ እማዬም ሥራዋን ትታ የኔን የቤት ሥራ መሥራት ትችላለች..

‹ትችላለች እኮ..ግን በሕይወት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች አሉ። ከዘገዩ የሚጎዱ..ከረፈዱ የማይጠቅሙ የሕይወት ገጾች። እስከ ማታ በመጠበቅህ ምንም አትሆንም..በመጠበቅ ውስጥ ትዕግስትን ትማራለህ፡፡

‹እሺ አንተ ንገረኝ..

‹ምን ልንገርህ?

‹ሀገር ማለት ምንድነው?

ብዙ ሳቆች ጠይም ፊቱ ላይ እየመጡ ይሄዳሉ። ከአባቱ ተጋብቶበት ስለ ሀገር ሲሰማ ደስ ይለዋል። ግን አባቱ ከነገሩት እውነት ውጪ የሚነግረው ሌላ እውነት የለውም። የአባቱ እውነት ለሁሉ የሚበቃ እውነት ነው። ሀገርን በተመለከተ..ኢትዮጵያዊነትን በተመለከተ እንደ አባቱ እውነት ያለው ሰው አያውቅም። ከትላንት እስከዛሬ በተረማመደባቸው የዘመን ሀዲድ ውስጥ ኢትዮጵያዊነትን ከነነፍሱና ከነቀለሙ ያገኘው በአባቱ ልብ ውስጥ ነው። ያኔ ልጅ ሆኖ ኢትዮጵያ አባቱን ትመስለው ነበር። ያኔ ልጅ ሆኖ ሀገር ሲባል የአባቱ መልክና መልካም ስብዕና ነበር የሚታየው። በሕይወቱ የማይረሳውና ዛሬም ድረስ የሚያስቀው አንድ እውነት አለ..እኛ ቤት ኢትዮጵያ አለች ብሎ የክፍል ጓደኞቹን ሰብስቦ ወደ ቤት ይዞ በመሄድ ከአባቱ ጋር አስተዋውቋቸው ያውቃል፡፡

‹ንገረኛ..እየጠበኩህ እኮ ነው? የልጁ ተማጽኖ ከሀሳቡ መነጠቀው፡፡

‹በሕይወት ዘመንህ ሁሉ የሚከተልህን የአባቴን እውነት ልሰጥህ ትላንቴም በመበርበር ላይ ነበርኩ። አባቴ ለእኔ እንደሰጠኝ ሁሉ አንተም ለልጆችህ የምሰጠው እውነት ነው። ከዚህ እውነት ውስጥ አንድ ሳታጎድል አደራዬን ለልጅ ልጆችህ እንድታስተላልፍ እፈልጋለሁ። ሀገር እኔና አንተ እና ደግሞ ሌላው ሰው ነው። ሀገር የእኔና የአንተ ደግሞም የሌላው ሰው መልክ ናት። ሀገር ከዚህ ቤት ስትወጣ የምታየው እውነት፣ የምትሰማው ዜማ ነው። ሀገር የእኛና የጎረቤቶቻችን የፍቅር..የአንድነት ጠርዝ ነው። በትላንት በዛሬና በነገ መካከል የተሳለ የአብሮነት አሻራ፡፡

‹የሀገር ፍቅርስ? ትንሹ ልጅ ጠየቀ፡፡

‹የሀገር ፍቅር ሀገርን ከማወቅና ከመረዳት የሚጀምር እውቀት ነው። የሀገር ፍቅር በሀገር እውነት ውስጥ መኖር ነው..በአንተ በኔና በሌላው ነፍስ ውስጥ ሕያው ሆኖ መብቀል። በዚህ እውነት ዓለምህን ገንባ.. በዚህ እውነት ቤትህን ሥራ..በዚህ እውነት ራስህን አሸንፍ፡፡

‹ለአስተማሪያችን ይሄን ከነገርኩት አስር ከአስር አገኛለሁ? ትንሹ ልጅ በመጓጓት ጠየቀ፡፡

‹ለአንድ ጊዜ ሳይሆን ለዘላለም የሚያኮራህን እውነት ነው የነገርኩህ ደግሞ የሁሉም ጥያቄ መልስ ሀገር ናት። ሀገርህን ስታውቅ ዓለምህን ታውቃለህ..የእውነት ስፍራው ይሄ ነው። በዚህ እውነት ውስጥ እንድትኖር እፈልጋለሁ። እውቀት ሁሉ፣ጥበብ ሁሉ፣ስልጣኔ ሁሉ ሀገርን ከማወቅ..ሀገርን ከመውደድ የሚጀምር ነው፡፡

ልጁ በአባቱ መልስ አስር ከአስር ሲያገኝ እያሰበ... በጓደኞቹ ፊት በኩራት ሲቆም..ሲጨበጨብለት እያሰበ ደስታ ወሰደው፡፡

‹የአባትን አደራ ለልጅ እንደመስጠት..የአባትን እውነት ለልጅ እንደመንገር..ሀገርን ለትውልድ እንደማውረስ ምን ትልቅ ስጦታ አለ? አባት እንዲህ እያሰበ ከጆንበሯ ጋር ወደ ቤቱ ገባ።

# ዓለም አቀፍ



## ቻይና ወደ ተለያዩ አህጉራት “የስለላ ፊኛዎችን” መላኳ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ቻይና ወደ ተለያዩ አህጉራት የስለላ ፊኛዎች መላኳ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ገለጹ፡፡

ዋይት ሀውስ ረቡዕ እለት እንዳስታወቀው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ፊኛዎችን ለስለላ ሥራዎች ወደ ተለያዩ ሀገራት መላክ የተጀመረ ሲሆን የዋይት ሀውስ ቃል አቀባይ ካረን ፒየር ፒየር በአምስቱ አህጉራት በሚገኙ ሀገራት ላይ ፊኛዎች ታይተዋል ብለዋል።

ቻይና በድርጊቷ የእነዚህን ሀገራት ሉዓላዊነት መጣሷን የምትገልጽ አሜሪካ፤ ከጥቂት ቀናት በፊት ይህንን የቻይና ተንሳፋፊ ፊኛ ተኩሳ መጣሏ ይታወሳል።

ቻይና በበኩሏ ለአየር ንብረት መረጃዎች እና ለሌሎች ሳይንሳዊ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ማዋሏን ተናግራለች፤ አሜሪካ በተንሳፋፊው ፊኛ ላይ ያደረሰችውን ወታደራዊ ጥቃት አውግዛለች፡፡


ጉዳዩን አስመልክታ ፊኛው በአሜሪካ አየር ክልል ውስጥ የገባው በስህተት ነው ብትልም የአሜሪካ ባለስልጣናት ግን ፊኛው ለስለላ ዓላማ መላኩን በግልጽ አስታውቀዋል፡፡

ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት ወደ ቤጂንግ አቅደው የነበሩት የአሜሪካ ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን በዚህ ምክንያት ጉዟቸውን መሰረዛቸው አይዘነጋም።

የቻይና ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተለያዩ ለመሰብሰብ በሚል ያሰማራቻቸው ፊኛዎች ከአሜሪካ በተጨማሪ ወደ ደቡብ እና ካሪቢያን የአየር የአየር ክልሎች መላካቸውንም አክለው ገልጿል።

## ቱርክ ለአደጋው የሰጠችው ምላሽ ክፍተት እንደነበረው ተጠቆመ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡ የቱርኩ ፕሬዚዳንት ራሲብ ጣይብ ኤርዶሃን በሀገራቸው ያጋጠመውን ርዕደ መሬት ተከትሎ የተሰጠው ምላሽ ክፍተት እንደነበረበት አስታወቁ።

ኤርዶሃን ምላሹ ክፍተት መኖሩ ቢያምኑም እንዲህ ዓይነት መጠነ ሰፊ አደጋ ይኖራል ብሎ መዘጋጀት አስቸጋሪ ነው ሲሉ መንግሥታቸውን ተከላክለዋል። በሁለቱ ርዕደ መሬቶች የሶሪያን ጨምሮ የሟቾች ቁጥር 15ሺህ ማለፉ እየተነገረ ይገኛል።

አንዳንድ ሰዎች ለአደጋ የተሰጠው ምላሽ በጣም ቀርፋፋ እንደ ነበር ጠቁመው፤ መንግሥትም በቂ ዝግጅት እንዳላደረገ የሰላ ትችት ሲሰነዝሩ ተደምጠዋል፡፡ ሆኖም ግን ኤርዶሃን መንግሥታቸው የነበረበትን ክፍተት ካስረዱ በኋላ አሁን ግን ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ እንደማይወጡ ማረጋገጫ ቢሰጡም በቱርክ የዋንኛው ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ እንደ ኩሉቺተሮሉ ያሉ ሰዎች በዚህ አይስማሙም።

ከማል “ለዚህ ቀውስ አንድ ሰው ተጠያቂ ይሆናል ካልን ያ ሰው ኤርዶሃን ነው” በማለት ጠንከር ያለ ትችት ሰንዝረዋል። ኤርዶሃን በበኩላቸው ይህን የከማል ኩሉቺተሮሉን ትችት እንደማይቀበሉት ነገር ግን ከእንዲህ ዓይነት አደጋዎች በኋላ አንድነት እንጂ የፖለቲካ ልዩነቶች ቅር እንዳይደሉ ተናግረዋል።

ይሁንና የሕዝብ ስቃይን ተገን አድርገው የፖለቲካ ትርፍ ለማጋበስ አሉታዊ አስተያየት የሚሰጡ ሰዎችን እንደማይታገሱም አስጠንቀቀዋል። በሺህ የሚቆጠሩ ከርዕደ መሬቱ አደጋ የተረፉ ዜጎች ለሦስተኛ ሌሊት ከባድ ቅዝቃዛ ባለበት ሁኔታ ጎዳና ላይ እያደሩ ነው።

ከፍርስራሹ ውስጥ ከዚህ በኋላ በሕይወት የሚኖሩ ይኖራሉ ወይ የሚለው ተስፋም እየከሰመ መጥቷል።

የዓለም ጤና ድርጅት በከፍተኛ ቅዝቃዜው የተነሳ የጤና ችግር የሚያጋጥማቸው በርካታ ከአደጋው የተረፉ ሰዎች እንደሚኖረ የተነበየ ሲሆን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፉን እንዲቀጥል ተማጽኗል።

በሶሪያ ሁኔታዎች ከቱርክ የከፉ ሲሆን በጦርነቱ በርካታ መሠረተ ልማቶች መውደማቸውን ተከትሎ ያለውን እርዳታም በበቂ ለማድረስ ፈተና ሆኗል።የአውሮፓ ኅብረት ሦስት ሚሊዮን ዩሮ ገደማ ለሶሪያ የአደጋ ጊዜ ምላሽ የለገሰ ሲሆን እርዳታው በአማጺዎች ለተያዙ አካባቢዎችም በመንግሥት እጅ ላሉትም እኩል እንዲደርስ አሳስቧል።

ዜና

# ዩኒቨርሲቲው አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየሰራ ነው

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የአርብቶና ከፊል አርብቶአደሩን ማኅበረሰብ ችግሮች የሚፈቱ የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና የማኅበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ኤልያስ አብዱላሂ ገለጹ።

ዶክተር ኤልያስ አብዱላሂ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ዩኒቨርሲቲው በግብርናው ዘርፍ በእንስሳት እርባታና በተለያዩ ዘርፎች አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩን ማኅበረሰብ የሚደግፉ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

ዩኒቨርሲቲው በምርምር ያስተዋወቃቸውን የበቆሎና የተለያዩ ምርጥ ዘሮች ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመሞከር ተደራሽ አድርጓል። በተለይም ከቀላ ስንዴ ጋር ተያይዞ ጅግጅጋ አካባቢ ያሉ አርብቶ አደሮች እንዲጠቀሙበት ተደርጓል።

120 አባወራዎችን በማኅበር በማደራጀት፣ ምርጥ ዘር በማቅረብና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አስተራረስ እንዲከተሉ በመደገፍ ወደ ምርታማነት እንዲገቡ እየሰራን ነው ያሉት ዶክተር ኤሊያስ፤ በእንስሳት ሀብት ልማት ደግሞ በሶማሌ ክልል የሚገኙ የግመል ዝርያዎች ላይ በዩኒቨርሲቲው አስተባባሪነት ጥናት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

በደገሀቡር አካባቢ የምርምር ማዕከል በማቋቋም የግመል ርባታና ማበልጸጊያ መርሀግብር ፕሮፖዛል ተነድፎ እንቀስቃሴ መጀመሩንም ምክትል ፕሬዚዳንቱ አመላክተዋል።

ዶክተር ኤሊያስ እንደገለጹት፤የእንስሳት ጤና ችግሮችን ለመቀነስ ዩኒቨርሲቲው በሶስት ወረዳዎች የእንስሳት ጤና ማዕከላትን በማቋቋም ህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲያገኝ አድርጓል።

ከአሜሪካው ቴክሳስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ግመሎችን የሚያጠቁ በሽታዎች ላይ ጥናትና ምርምር ለመስራት ጥረት እየተረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

በድርቅ ምክንያት የሚጎዱ ከብቶችን መጠን ለመቀነስም አርብቶአደሩ የተመረጡ የመኖ ዝርያዎችን በራሱ መንገድ ማልማት እንዲችል የአቅም ግንባታ እና የተሞክሮ ሥራዎች ላይ በዩኒቨርሲቲው የመስክ ላይ ድጋፍ ይደረጋልም ነው ያሉት።

የግመል ወተትና ሥጋ በተለይ በአረብና ገልፍ አካባቢ ሀገራት ፍላጎቱ ከፍተኛ መሆኑን በመግለጽ ምርታማነቱን የማሳደግ ስራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

ዩኒቨርሲቲው በሶማሌ ክልል፣ በቦረና እና በአፋር አካባቢ የሚገኙ የሀገራችን የግመል ዝርያዎች እና የጄኔቲክስ ባህሪያቸውን በማጥናት ሳይንሳዊ ምርምር እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል። በድርቅ ምክንያት የሚኖሩ ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም በአጠቃላይ እንስሳትን በወተትና ሥጋ ውጤታማነታቸውን በማሻሻልና ለአካባቢው ማኅበረሰብ የማሰራጨት ስራዎችም እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

በዩኒቨርሲቲው በክልሉ መንግሥትና ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በወተት ምርታቸው ዝቅተኛ የሆኑትን የወተት ከብቶች ዝርያቸውን የማዳቀልና የወተት ምርታማነታቸውን የማሳደግ ሥራ ተሰርቷል ሲሉ አስረድተዋል።

በተለይ ድርቅ ባለባቸው አካባቢዎች ዝቅተኛ የሆነውን የወተት ምርት ለማሳደግ በቀን ከአንድ ላም ከሰባት እስከ 10 ሊትር ወተት ለማግኘት የሚያስችል የዝርያ ማሻሻል ስራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲው በስሩ በሚገኙ አምስት ኢንስቲትዩትና አምስት ኮሌጆች አማካኝነት በክልሉ ያለውን የትምህርት ተደራሽነት ክፍተት ለመሙላት በ11 ዞኖች የመማር ማስተማር ሂደትን የሚያሳድጉ ማዕከላትን ከፍቷል ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው ለትምህርት ቤቶች የሚሆኑ ላብራቶሪዎችን በማደራጀትና የተለያዩ የመማሪያ ቁሳቁሶችን ድጋፍ በማድረግ አርብቶ አደሩ ማኅበረሰብ የዘመናዊ ትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆን ጥረት እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

ከድርቅና ውሃ እጥረት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ የማኅበረሰብ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚረዱ ባህላዊ የግጭት አፈታቶች ላይ ጥናት በማድረግ በይበልጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የግንዛቤ ስራ እየተከናወነ መሆኑን ዶክተር ኤሊያስ አስረድተዋል።

በ1999 ዓ.ም የተቋቋመው ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ከ25 ሺህ በላይ ተማሪዎችን እያስተናገደ ይገኛል። ከዚህ ባለፈ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የማኅበረሰብ አገልግሎቶቹን እያሳደገ ይገኛል።

## «የዓባይ ግድብ ቱር»...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ግንባታውን 89 በመቶ ማድረስ ችለናል ብለዋል።

እንደ ዶክተር አረጋዊ ገለጻ፤ የዓባይውን ግድብ ለማጠናቀቅና ቀሪውን 11 በመቶ ስራ ለማጠናቀቅ 60 ቢሊየን ብር ያስፈልጋል። ስለሆነም ኅብረተሰቡ በተለመደው ትብብር ድጋፉን በማጠናከር ግድቡን ለማጠናቀቅ የጀመረውን ጥረት እንዲያጠናክር ዶክተር አረጋዊ ጥሪ አቅርበዋል።

የታላቁ የኢትዮጵያ ዓባይ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ከኢትዮጵያ ታሪክ ባህል እና ቅርስ አድን በጎ አድራጎት ድርጅት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው "የዓባይ ግድብ ቱር" የጉዞ መርሐ-ግብር በመላው የሀገሪቱ ከተሞች ይካሄዳል ያሉት ዶክተር አረጋዊ፤ ሁሉም ማኅበረሰብ በገቢ ማሰባሰቢያው ላይ ሊሳተፍ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ ዓባይ ግድብ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ምስክር ነጋሽ በበኩላቸው፤ በመዲናዋ የዓባይ ግድብ ግንባታ ላይ በርካታ ሕዝባዊ ተሳትፎዎች መደረጋቸውን አስታውሰው፤ በቀጣይም በሚከናወነው መርሃግብር የመዲናዋ ነዋሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

የዓባይ ግድቡ ከተጀመረበት 2003 ዓ.ም ጀምሮ በመዲናዋ በተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ መንገዶች ከ4 ነጥብ 25 ቢሊዮን በላይ ብር መሰብሰቡን አስታውቀዋል።

በተለይም ከ2010 ዓ.ም በኋላ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ኅብረተሰቡ ድጋፉን አጠናክሯል ያሉት አቶ ምስክር፤ በ2013 ዓ.ም ብቻ ከ2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን ገልጸዋል።

በ2015 በጀት ዓመት ስድስት ወራት 354 ነጥብ 4 ሚሊየን ብር በላይ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን ። በአጠቃላይ ከመዲናዋ 4 ቢሊዮን 256 ሚሊዮን 855 ሺህ ብር በላይ ተሰብስቧል ብለዋል።

በቀጣይም ግድቡ ተጠናቆ አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት እስኪጀምር ሕብረተሰቡን በማሳተፍ የገቢ ማሰባሰብ ስራው እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የዩኒቨርቲው ድጋፍና ያስገኘው ውጤት

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

ባሳለፍነው ወር አጋማሽ የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤት ይፋ መደረጉ ይታወሳል። በዚህ ውጤት መሰረት ሰባት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ሙሉ ለሙሉ ያሳለፉ ሲሆን አንድ ሺ 161 ትምህርት ቤቶች ደግሞ ምንም ተማሪ አለማሳለፋቸውን ትምህርት ሚኒስቴር መግለፁ ይታወሳል። ተማሪዎቻቸውን ሙሉ ለሙሉ ካሳለፉ ሰባት ትምህርት ቤቶች መካከል በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ የሚተዳደረው የቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሸርድ ካምፓስ አንዱ ነው።

ትምህርት ቤቱ የተጀመረው እንደ ፕሮጀክት ብቃት ያላቸውን የተለያዩ ተማሪዎች ሰብስቦ የማስተማር ፕሮጀክት ነበር። ይህ ፕሮጀክት ግን ከሁለት አመት በኋላ ቆመ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ትምህርት አልጨረሱም ነበርና ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ እነዚህ ተማሪዎች ሁለት አመት ተምረው የአስረኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና ተፈትነው መበተን የለባቸውም በማለት ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመሆን ዩኒቨርሲቲው ከሚመደብለት በጀት ላይ መምህራንን ቀጥሮ ማስተማር ጀመረ።

ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ እና ከአራዳ ክፍለ ከተማ ጋር በመካከርም ራሱን የቻለ ካምፓስ ያስፈልገዋል በማለት በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የነበሩ ላብራቶሪዎች አመጥቶ አሁን ትምህርት በቋሚነት በሚሰጥበት የቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሸርድ ካምፓስ በመትከል አዲስ ካምፓስ ለመፍጠር ቻለ። በዚህ ረገድ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ተግባር የሚደነቅ ነው። ትልቅ አቅም ያላቸው በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች በሀገራችን ይገኛሉ፤ እንደ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ ሁሉ እነዚህም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በትምህርቱ ዘርፍ ተሳትፎ ማድረግ ቢችሉ በዘርፉ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል።



**አቶ አቤል ጫላ**

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከዚህ የበለጠ ስራ መስራት ይችላል የሚል እምነት አለኝ የሚሉት በኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የሚተዳደረው የቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሸርድ ካምፓስ ፕሪንሲፓል የሆኑት አቶ አቤል ጫላ ናቸው። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 6 ኪሎ ካምፓስ፣ ASTU፣ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲና ሌሎች ተቋማትም ተባብረው ቢሰሩ በትምህርት ዘርፉ ትልቅ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ። የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ልምድ ወደ ሌሎች ሊስፋፋ ይገባል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ ካምፓሶቹ እነዚህን ትምህርት ቤቶች ቢከፍት ከተለያየ ርቀት ላይ የሚመጡ ተማሪዎችን ማስቀረት ይችላል። ከበጀት አንፃር ሲንመለከት ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ የሚመደብለት በጀት ከሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች አንፃር አነስተኛ ነው፤ ከዚያው ላይ ቀንሶ አስተማሪዎች ቀጥሮ ተማሪዎችን እያስተማረ ይገኛል፤ ሌሎች ትላልቅ ዩኒቨርሲቲዎች ከዚህ በላይ ማድረግ ይችላሉ።

ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ሚኒስቴር ስር ያለ መሆኑን የሚያስረዱት አቶ አቤል፤ እስካሁን ባለው ሁኔታ ከበጀቱ ላይ ድጋፍ እያደረገ የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበልና የትምህርት አቅማቸው እያደገ እንዲመጣ አድርጓል። በዚህም ከትምህርት ሚኒስቴር ቀና ምላሽ ማግኘት ተችሏል። በትምህርት ሚኒስቴር ድጋፍ ላቦራቶሪዎች በመደራጀት ላይ ናቸው። የኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ አመራሮችም በተለያየ ጊዜ ሳይንስ ሼርድ ካምፓስን እንደሚያስተዋውቁና ዩኒቨርሲቲው የመማሪያ ግቢውን ለተማሪዎች ምቹ ለማድረግ በራሱ በጀት ስራዎች ማስጀመሩን ይናገራሉ።

ትምህርት ቤቱ እስካሁን አራት ጊዜ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለሀገር አቀፍ ፈተና ያቀረበ ሲሆን አራቱንም ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ተማሪዎቹን ለማሳለፍ ችሏል። በተማሪዎቹ መካከል የውጤት ልዩነት ይስተዋላል እንጂ የመውደቅ ስጋት አጋጥሟቸው አያውቅም። የዚህ ትምህርት ቤት መምህራንም ሆኑ አመራሮች የሚያሳስባቸው በሀገር አቀፍ ደረጃ ምን ያህል ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ሊያመጡ ይችላሉ የሚል ጉዳይ እንጂ ምን ያህል ተማሪ ሊወድቅ ይችላል የሚል ሃሳብ አይደለም። የ2013 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ የፈተና ውጤት ብንመለከት 78 ተማሪዎችን ያስፈተነው ትምህርት ቤቱ 42 ተማሪዎች 600ና ከዚያ በላይ ውጤት ሲያመጡ፤ ዝቅተኛው ውጤት 529 ነበር፤ የአመቱ ከፍተኛ ውጤትም የተመዘገበው በዚህ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበር።

የመምህራን ቅጥር የሚካሄደው በዩኒቨርሲቲው አማካኝነት ሲሆን በዩኒቨርሲቲ መምህራን ደረጃ፤ ሁለተኛ ዲግሪና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራንን እንቀጥራለን የሚሉት አቶ አቤል ጫላ፤ መምህራን በሚጓደሉበት ወቅት ደግሞ የዩኒቨርሲቲው መምህራን እንዲያስተምሩ ይደረጋል። ትምህርት ቤቱ የመንግስት ትምህርት ቤት ነው፤ ሲለዚህ የምናስተምረው በመንግስት ካሪኩለም መሰረት ነው። ለተማሪዎቻችን የምንሰጠው የተለየ ትምህርት አይኖርም። የምንጠቀመው ትምህርት ሚኒስቴር የሚያዘጋጀውን የመማሪያና የማስተማሪያ መፃህፍት ነው። ተማሪዎቹ ፈጣን በመሆናቸው አንዳንዴ መምህራኑ ተጨማሪ የማጣቀሻ መፅሃፍትን ሊጠቀም ይችላሉ በማለት ያስረዳሉ።

እንደ ፕሪንሲፓሉ ገለፃ፤ የዩኒቨርሲቲው አመራሮች የሚያደርጉት ክትትልና ድጋፍ የትምህር ቤቱ ውጤታማነት ምንጭ መሆን ችሏል። ተማሪዎቹ ፈተና ላይ ከመቀመጣቸው በፊት የኮተቤ ዩኑቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶክተር ብርሃነመስቀል ጠና በአካል ተገኝተው ተማሪዎች የስነ-ልቦና ዝግጅት እንዲኖራቸው የተለያዩ ልምዶችን አካፍለዋቸዋል።

ዩኒቨርሲትዎች ሲመሰረቱ ሶስት ስራ ተሰጥቷቸዋል፤ የመጀመሪያው መማር ማስተማር ነው፣ ሁለተኛ ጥናትና ምርምር ማድረግ ነው፣ ሶስተኛው ደግሞ የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት ነው። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ተባብረው ሲሰሩ በጎ አድራጎት ከመሆኑ ባሻገር ማህበራዊ ሃላፊነታቸውን እየተወጡ ነው ማለት ነው። ከዚህ አንፃር ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲት ተልዕኮውን እያሳካ ነው፣ ማህበረሰቡን እያገለገለ ማህበራዊ ሃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል። ልጆችን እያስተማረ የሚገፈልጉት ደረጃ ላይ እያደረሰ ነው። ይህ ለሌሎችም ጥሩ ተምሳሌት የሚሆን ስራ ነው። ሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም እንደዚህ አይነት ስራዎችን በሌሎች ተቋማት ላይ መስራት ቢችሉ የኢትዮጵያን ከቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙና ሌሎች የተወሳሰቡ ማህበራዊ ችግሮችን መፍታት የሚችሉ ዜጎች ከማፍራት አንፃር ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል በማለት ያብራራሉ።

# ስፖርት





# ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በድል የደመቁበት የቤት ውስጥ ውድድር

ብርሃን ፈይሳ

በተለያዩ ዓለማት የጎዳና እና የመም ውድድሮች ላይ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከአሸናፊነት ባለፈ ፈጣን ሰዓት ማስመዝገባቸው የተለመደ በመሆኑ በዚያው ልክ ውድድሮቻቸው በጉጉት ይጠበቃሉ። በዚህ ወቅት እየተካሄዱ ባሉት የቤት ውስጥ የዙር ውድድሮች ላይም በተመሳሳይ አዳዲስ ክብረወሰኖችን ያስመዘግባሉ በሚል የአትሌቲክስ ቤተሰቡ በቅርበት ይከታተላቸዋል።

ከነዚህ ውድድሮች መካከል ከትናንት በስቲያ ምሽት የተካሄደውና በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ በተሰጠው የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች አስደናቂ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችለዋል።

በፖላንዷ ቱሪን በተለያዩ ርቀቶች ከተካሄዱት ውድድሮች መካከል አስቀድሞ ሰፊ ትኩረት ያገኘው የአንድ ማይል የሴቶች ፉክክር ነው። በዚህ ውድድር የዓለም ክብረወሰን ታሻሽላለች ተብላ ስትጠበቅ የነበረችው ገድሞ የዓለም ቻምፒዮና አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ ስትሆን በርቀቱ ሁለተኛውን የዓለም ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ ማሸነፍ ችላለች። በዙር እየተካሄደ በሚገኘው በዚህ ውድድር እአአ በ2021 በፈረንሳይ ሌቪን በ1ሺ500 ሜትር የተካፈለችው ይህቺ ድንቅ ኢትዮጵያዊት አትሌት 3:53.09 በሆነ ሰዓት ርቀቱን በማጠናቀቅ የዓለም ክብረወሰኑን መስበሯ የሚታወስ ነው። ባለፈው ዓመት በሰርቢያ ቤልግሬድ በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ላይም በዚሁ ርቀት የተካፈለችው ጉዳፍ 3:57.19 በሆነ ሰዓት በመግባት ሁለተኛውን ፈጣን ሰዓት ማስመዝገቧ ይታወሳል።

በዚህ ውድድር ላይ ስትካፈልም በአንድ ማይል በሀገሯ ልጅ ገንዘቤ ዲባባ ለዓመታት ተይዞ የቆየውን ክብረወሰን የግሏ ለማድረግ ነበር። ነገር ግን 4:24.98 በሆነ ሰዓት ርቀቱን በማጠናቀቅ በሰከንዶች ልዩነት ሁለተኛውን ፈጣን ሰዓት ልታስመዘግብ ችላለች። የክብረወሰኑ ባለቤት የሆነችው ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት ገንዘቤ ዲባባ ርቀቱን 4:13.31 የሆነ ሰዓት በመሮጥ ቀዳሚውን ሰዓት የያዘች ሲሆን፤ እአአ በ2016 ነበር ክብረወሰኑን በስማ ያስመዘገበችው። የ5ሺ ሜትር የዓለም ቻምፒዮኗ እንዲሁም የ1ሺ500 ሜትር የብር ሜዳሊያ ባለቤቷ ጉዳፍ በዚህ ውድድር ላይ 400 ሜትሩን የሮጠችው በ1ደቂቃ ከ1 ሰከንድ ከ 1ማይክሮ ሰከንድ ነው። በድንቅ አሯሯጧ ዓለምን ያስደመመችው ጉዳፍ ተከትለዋት ከገቡት ተፎካካሪዎቿ ጋር የነበራት ልዩነትም ፈጣኑን ሰዓት ልታስመዘግብ ትችላለች በሚል እንድትጠበቅ አድርጋት ነበር። ያም ሆኖ በሽርፍራፊ ሰከንዶች በመዘግየቷ ዓለምን ለጥቂት ከእጇ ሊወጣ ችሏል።

ይህንን ተከትሎም የ26 ዓመቷ ወጣት አትሌት ‹‹ያቀድኩት የዓለም ክብረወሰንን ለመስበር ነበር፤ ሆኖም አትሌቲክስ እንዲህ ነው። በልምምድ ወቅት ጥሩ አቋም ላይ እንዳለህ ሊሰማህ ይችላል፤ ነገር ግን በውድድር የፈለከውን ማግኘት አትችልም። ቢሆንም አሁንም የማስበው ይህ ክብረወሰን አንድ ቀን የእኔ እንደሚሆን ነው›› ስትል መግለጿን የዓለም አትሌቲክስ በድረ ገጹ አስነብቧል። ጉዳፍን ተከትላ የገባቸው ፖላንዳዊቷ አትሌት ቬሮኒካ ሊዛኮውስካ 4:29.06 የሆነ ሰዓት ስታስመዘግብ፤ ጃማይካዊቷ አዴሌ ትሬሲ ደግሞ 4:30.17 በሆነ ሰዓት ውድድሩን በሶስተኝነት መፈጸም ችላለች።



አትሌት ጉዳፍ ፀጋይ በአንድ ማይል የቤት ውስጥ ውድድር ሁለተኛውን የዓለም ፈጣን ሰዓት አስመዝግባለች፣

ሌላው በጉጉት ሲጠበቅ የቆየው የ3ሺ ሜትር ሴቶች ውድድር ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከአንድ እስከ አራት ያለውን ደረጃ በማስመዝገብ በፍፁም የበላይነት አጠናቀዋል። በዚህ ውድድር ሌላው አስደናቂ ነገር ደግሞ በአትሌቶቹ መካከል የነበረው የፉክክር ስሜት ነው። ርቀቱን በቀዳሚነት ያጠናቀቀችው አትሌት ፍሬወይኒ ኃይሉ ከ800 ሜትር አንስቶ አስደናቂ በሆነ ታክቲክ ሩጫውን መምራት የጀመረች ሲሆን፤ የሀገሯ ልጆችም ተከትለዋት በመግባት አስደሳቹን ድል አጣጥመዋል። ባለፈው ዓመት በሰርቢያዋ ቤልግሬድ አስተናጋጅነት በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ለሀገሯ በ800 ሜትር የብር ሜዳሊያ ያስመዘገበችው ፍሬወይኒ በ3ሺ ምትርም አስደናቂ ብቃቷን ለዓለም ልታሳይ ችላለች። ርቀቱን አጠናቃ የመጨረሻዋን መስመር ለመርገጥም የፈጀባት 8:46.92 የሆነ ሰዓት ነው።

በቤት ውስጥ ቻምፒዮናው በዚህ ርቀት የነሃስ ሜዳሊያ ባለቤት የነበረችው ሌላኛዋ አትሌት እጅጋየሁ ታዬ በአንድ ሰከንድ ብቻ በመዘግየት (8:47.81) ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ልታጠናቅቅ ችላለች። በቤልግሬዱ ቻምፒዮና የዚህ ርቀት የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት የነበረችው አትሌት ለምለም ኃይሉ፣ በዚህ ውድድር ሶስተኛ ሆና ስታጠናቅቅ የገባችበት ሰዓት 8:49.10 ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም ሰዓት ቻምፒዮን ከሆነችበት በ8 ሰከንዶች የዘገየ ነው። በኦሪጎኑ የዓለም ቻምፒዮና በ3ሺ ሜትር መሰናክል የብር ሜዳሊያ ያገኘቻው የወርቅውሃ ጌታቸው ደግሞ አራተኛዋ አትሌት በመሆን ውድድሩን ፈጽማለች።

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 10/2015

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ በአማራ ክልል በጦርነት የተጐዱ አካባቢዎችን መልሶ ማቋቋም ግንባታ ፈንድ ጽ/ቤት ማስፈፀሚያ ከተመደበው በጀት ለኮምቦልቻ እጽዋት ላብራቶሪ ዕቃዎች ሪኤጀንት ግዥ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች መወዳደር የሚችሉ መሆኑን ያሳውቃል።

1. በዘርፉ እና በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ማቅረብ የሚችሉ፣
3. የግዥ መጠኑ ከብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) እና ከዚያ በላይ ከሆኑ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ/ቫት/ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. በቀረበው ዝርዝር መግለጫ /Specification/እና ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ አሸናፊ ከተለየ በኋላ አሸናፊው ሙሉውን ዕቃ ከማቅረቡ በፊት ናሙና ማቅረብ አለበት፡፡
5.ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ በተ.ቁ 1-3 የተጠቀሱትንና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለሚወዳደሩበት ዕቃ 2% እና ጨረታውን ካሸነፉ በኋላ ለውል ማስረከቢያ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ 25% በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በማይሻር ሌተር ኦፍ ክሬዲት የቀረበ ዋስትና ጥሬ ገንዘብ ወይም የተረጋገጠ ቼክ ወይም የክፍያ ትዕዛዝ ለስድስት ወር ማስያዝ የሚችሉ፣
7. ማንኛውም ተጫራቾች የጨረታ ሀሳቡን ቴክኒካል ዶክመንትና የዋጋ ማቅረቢያ (ፋይናሽያል ዶክመንት) ዋና እና ቅጅ በማለት በተለያየ ፖስታ አሽጐ በግብርና ቢሮ የግብርና ግብአት ገጠር ፋይናንስ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 18 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዘወትር በሥራ ሰዓት ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 16ኛው ቀን 4.00 ሰዓት ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
8. በጨረታው ለመሣተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 100.00/አንድ መቶ ብር/ በመክፈል አብክመ ግብርና ቢሮ ቢሮ ቁጥር ማግኘት ይችላሉ፡፡
9. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግብርና ቢሮ የግብርና ግብአት ገጠር ፋይናንስ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 018 በ16ኛው ቀን 2015 ዓ.ም 4:30 ሠዓት ይከፈታል፡፡
10.ቢሮው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
11.በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ስለጨረታው ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ ቢሮ ቁጥር 18 ድረስ በአካል ወይም በፋክስ ቁጥር፡- 0582208771/ በመላክ በስልክ ቁጥር፡- 0582205849/7048 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፣
12. በማስታወቂያ ያልተገለፁ ነገሮች ቢኖሩም በግዥ መመሪያው መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል።
13.የጨረታውን ማስታወቂያ በቢሮው ድረ-ገጽ Web site Address/WWW.amhboard gov.et መከታተል ይቻላል።

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ**
**ባህር ዳር**

## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 01/2015

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጉለሌ ክ/ከተማ ት/ፅ/ቤት ወረዳ 01 ስር የሚገኘው የድል በትግል የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ለ2015 ዓ.ም በድጎማ በጀት ለት/ቤቱ አገልግሎት የሚውል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

ሎት 1 ፡-የትምህርት እቃዎች ብር 1,404
ሎት 2፡- ቋሚ እቃዎች ብር 1,404

በዚህ ጨረታ ለመወዳደር የምትፈልጉና ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች የምታሟሉ ህጋዊ

**ተወዳዳሪዎች፡-**

1. በመንግስት ዕቃ አቅራቢነት ዝርዝር የተመዘገቡ የምስክር ወረቀት ያላቸው እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ፡-
2. በዘመኑ የታደሰ የመንግስት ፈቃድ ያላቸው፤
3. የእቃዎች ዋጋ 15% ቫት ተጨምሮ ይቅረብ ባይቀርብ እንደተጨመረ ሆኖ የሚሰራ ይሆናል፡፡
4. ተጫራቾች የማይመለስ 100 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል የጨረታውን ዝርዝር መረጃ የያዘ ሰነድ ከት/ቤቱ ፋ/ግ/ን/አስ/ደጋፊ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 4 በመምጣት መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
5. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ በገዙት ሰነድ ላይ ባለው የዋጋ ማቅረቢያ ቦታ በግልፅ መሙላት አለባቸው፡፡
6. ተጫራቾች ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን በየሎቱ የጨረታ ማስከበሪያ ብር በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝ አለባቸው፡፡
7. ተጫራቾች የተመረጡ እቃዎች እና ናሙና ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ማቅረብ አለባቸው፡፡
8. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 (አስር) ተከታታይ የስራ ቀናት ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀ ሳጥን በቢሮ ቁጥር 02 ማስገባት ይችላሉ፡፡
9. አሸናፊ ሆነው የተመረጡ ድርጅቶች የአሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ የውል ማስከበሪያ ማቅረብ አለባቸው፡፡
10.አሸናፊው ተጫራች ያሸነፈባቸውን እቃዎች በራሳቸው የትራንስፖርት ወጭ ት/ቤቱ ንብረት ክፍል ድረስ ማምጣት አለባቸው፡፡ ት/ቤቱ ተጨማሪ በእቃዎች ላይ 20% የመጨመር ወይም የመቀነስ መብት አለው፡፡
11.ጨረታው ማስታወቂያው በወጣ በ10ኛው ቀን 11፡30 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ በ3፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎች ቢገኙም ባይገኙም ቢሮ ቁጥር 02 የሚከፈት ይሆናል፡፡
12.ት/ቤቱ የተሻለ መንገድ /አማራጭ/ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡- ጉለሌ ክ/ከተማ ሽሮሜዳ ከስፔን ኤምባሲ አጠገብ**
**ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር፡- 0111-54-20-95**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጉለሌ**
**ክ/ከተማ ት/ፅ/ቤት**